ምዕራፍ ፱

ጉባኤ

፩፤ ወኮነ በቀዳሚሁ በ፴ወ፫ቱ ኢዮቤልው፤

በሠላሳ ሶስተኛው ኢዮቤልዩ በመጀመሪያው እንዲህ ሆነ፤

ወከፈልዋ ለምድር ፫ተ መክፈልተ

ለሴም ወለያፌት ወለካም በበርስ ቶሙ፤

በየርስታቸው ለሴም ለያፌት ለካም ልትሆን ምድርን ከሦ ስት ከፈሏት፤ ፋሌክ ራግውን በስሳ አንድ ወልዶታል፤ ቢያ ገናኙት ሽሕ ከስድት መቶ ሃያ ስምንት ይሆናል። ይህ ሠላሳ ሶስት ኢዮቤልዩ ሆኖ ዐሥራ አንድ ዘመን ይተር ፋል፣ በሱባዔ ቢገቡት አንድ ሱባዔ ሆኖ ዐራት ዘመን ይተርፋል፤

በቀዳሚ ዓመቱ ዘአሐዱ ሱባዔ፤

ሱባዔ በሚደረግበት በመጀመ ሪያው ዓመት፤

እንዘ ይነብር ፩ዱ እምኔነ እለ ተፈኖነ ኀቤሆሙ፤

ወደርሳቸው ከተላክነ ከኛ

አንዱ መልአክ ተቀምጦ ሳለ፤

ወጸውአ ደቂቆ፣

ልጆቹን ጠራ፤

ወቀርቡ ኀቤሁ እሙንቱ ወውሉ ዶሙ፤

እነርሱም ልጆቻቸውም ወደ ርሱ ቀረቡ፤

ወከፈሉ ምድረ በዑፃዌ ዘይእኅዙ ሠለስቲሆሙ ውሉዱ፤

ሦስቱ ልጆቹ የያዙትን በዕጣ ተካፈሉ፤ አንድም ይዘውት የሚኖሩ ምድርን ተካፈሉ፤

፪፤ ወሰፍሑ እደዊሆሙ፤

እጃቸውን ዘረጉ፤

ወነሥኡ መጽሐፈ እምሕፅነ ኖኅ አቡሆሙ፤

ከአባታቸው ከኖኅ እጅ መጽ ሐፉን ተቀበሉ፤

ወወፅአ በመጽሐፍ ዕፃሁ ለሴም ማዕከለ ምድር ዘይእኅዝ በርስቱ፤

ርስት አድርጎ የሚይዘው የሴም ዕጣው በመጽሐፍ በም ድር መካከል ወጣ፤

ወለውሉዱ፤

ለልጆቹም ወጣ፤

ወለትውልደ ትውልድ ዘለዓለም።

ለዘለዓለሙ ለልጅ ልጅ ዘመን ሊሆን።

እማእከለ ደብረ ራፋ።

ከደብረ ራፋ ጀምሮ።

እሙፃኣ ማይ እምፈለገ ጢና።

የውሀ መውጫ ከሚሆን ከጢና ወንዝ ጀምሮ። አንድም ጢና ርሽ ይላል ከጢናርሽ ጀምሮ።።

፫። ወየሐውር መክፈልቱ መንገለ ዓረብ እንተ ማእከሉ ለዝ ፈለግ።

ይበጽሕ ሲል ነው ዕጣው በዚህ ወንዝ መካከል እስከ አለው ምዕራብ ይደርሳል።።

፬። ወየሐውር እንተ ሶበ ይቀርብ ኀበ ማየ ቀላያት እምኀበ ይወጽእ ዝንቱ ፈለግ እምኔሃ።

ይህ ወንዝ ከሚወጣበት ጀምሮ እስከ ጥልቁ ውሀ እስኪቀርብ ድረስ።

ወይክዑ ማያቲሆሙ ውስተ ባሕረ ሚአት።

ውሀዎችን ከዚያው ከሚአት ወንዝ ያፈሳል።

ወየሐውር ዝንቱ ፈለግ እስከ ባሕር ዓቢይ።

ይህ ወንዝ እስከ ኤርትራ ባሕር ይደርሳል።

ወኵሉ ዘመንገለ ገጸ ደቡብ ለያ ፌት።።

በደቡብ በኩል ያለው ሁሉ ለያፌት ደረሰ።

ወኵሉ ዘመንገለ ገጸ ሰሜን ለሴም።

በሰሜን በኩል ያለው ሁሉ ለሴም ደረሰ።

ወየሐውር እስከ ሶበ ይቀርብ ከራሶ።

ይበጽሕ ሲል ነው። እስከ ኮራሶ አጠገብ ይደርሳል።

ዘውእቱ ውስተ ሕፅነ ልሳን ።

ይኸውም በልሳነ ግብጽ ውስጥ ያለ ነው።

እንተ ትኔጽር መንገለ ሰሜን።

በሰሜን በኩል የምትነጣጠር።

ወየሐውር መክፈልቱ እንተ መን ገለ ባሕር ዓቢይ።

ዕጣው እስከ ኢያሪኮ ይደር ሳል።

ወየሐውር ርቱዐ። እስከ ይቀርብ መንገለ ዓረቢሃ ለልሳን።

በልሳነ ግብጽ ምዕራብ በኩል እስኪቀርብ ድረስ።

እንተ ትኄጽር መንገለ ሰሜን፤

በሰሜን በኩል የምትነጣጠር፤

እስመ ዛቲ ባሕር ልሳነ ብሔረ ግብጽ፤

የኤርትራ ስሟ ልሳነ ባሕረ ግብጽ ትባላለችና።

፫፤ ወትገምጽ እምዛየ መንገለ ሰሜን ትቀርብ፤

ትጸንዕ ሲል ነው፤ ከኤርትራ ባሕር አንስታ ወደሰሜን የምታደርስ ናት፤

መንገለ አፋሃ ለባሕር ዓባይ ውስተ ከንፈረ ማያት፤

በኤርትራ በመግቢያዋ በኩል አድርጋ ወደ ውሀው ዳር የምትወስድ ናት፤

ወተሐውር መንገለ ዓረበ ዓፈራ፤

ከዚያ አንስታ አፈራ ከሚባል ምዕራብ ድረስ ትደርሳለች።

ወተሐውር እስከ ትቀርብ ኀበ ማየ ግዮን ፈለግ፤

ግዮን ወደሚባለው ወንዝ ወደ ሰሜኑ ትደርሳለች፤

ወመንገለ ሰሜኑ ለማየ ግዮን መን ገለ ድንጋጉ ለዝ ፈለግ፤

በዓባይ ወንዝ በዳር በዳር በኩል አድርጋ፤

፮፤ ወተሐውር መንገለ ጽባሕ፤

ወደ ሰሜን የምትወስድ ናት፤

እስከ ሶበ ትቀርብ ኀበ ገነተ ኤዶም፤ መንገለ ሰሜኑ ለሰሜን፤

ቀኝ ቀኙን እያደረገች ኤዶም ገነት እስከ ሚባል እስክትደ ርስ ድረስ፤

ወእምጽባሒሃ ለዙላ ምድረ ኤዶም ፤

ከኤዶም ገነት ምሥራቅ አን ስታ፤

ወለዙሉ ጽባሒሃ፤

በገነት ካለው ምሥራቅ አን ስታ፤

ወይትመየጥ ኀበ ጽባሕ/

ከአንዱ ምሥራቅ ታደርስአ ለች፤

ወይመጽእ እስከ ይቀርብ መንገለ ጽባሒሁ ለደብር ዘስሙ ራፋ፤

ዳግመኛም ከአንዱ ምሥራቅ አንስታ ራፋ ከሚባል ተራራ እስከ ምሥራቁ ትደርሳለች፤

ወይወርድ መንገለ ጽንፉ ለሙጻአ

ጢና ፈለግ፤

ከዚያም አንስቶ ጢና ከሚፃ ለው ወንዝ ወደመውጫው ዳርም ይደርሳል።

፲፤ ላቲ መክፈልት ወጽአት በዕ ፃሁ ለሴም፤

አሁን የተናገርነው ሀገር ሁሉ በዕጣ ለሴም ደረሰው፤

ወለውሉዱ ለእኂዞታ ለዓለም፤

ለዘለዓለም ልጆቹ ይዘዋት ይኖሩ ዘንድ፤

ወለትውልዱ እስከ ለዓለም፤

የልጅ ልጆቹ እስከ ዘለዓለም ይዘውት ይኖሩ ዘንድ ዕጣ ወጣች፤ አሁን እንደ ተደተና ርነው ሁሉ በዕጣ ደረሰው፤

ወተፈሥሐ ኖኅ፤

ኖኅም ደስ አለው፤

እስመ ዝንቱ መክፈልቱ ለሴም ወለውሉዱ፤

የኢየሩሳሌም መንገል መንሿ እድል ፈንታ ሁና ለሴም ለል ጆቹ ደርሳለችና ደስ አለው፤

፲፩፤ ወተዘከረ ኵሉ ዘነበበ በአፉሁ በትንቢቱ ፤

ኖኅ በአንደበቱ የተናገረውን ትንቢት አሰበ፤

እስመ ይቤ ይትባረክ እግዚአብ ሔር አምላኩ ለሴም፤

የሴም ፈጣሪ እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን ብሏልና፤

ወይኅድር እግዚአብሔር ውስተ ማኅደሩ ለሴም፤

እግዚአብሔር በሴም ድንኳን ይደር ማለት ከሴም በተወለደ በአብርሃም ይደር ማለት ነው፤

ወለእመረ ከመ ገነተ ኤዶም ቅድ ስተ ቅዱሳን፤

ኤዶም የምትባል ገነት ከተከ በሩት የተከበረች እንደሆነች አወቀ፤

ወማኅደሩ ለእግዚአብሔር ውእቱ፤

የእግዚአብሔር ማደሪያ እንደ ሆነች አወቀ፤

ወደብረ ሲና ማዕከለ ገዳም፤

ደብረ ሲናም በምድረ በዳ መካከል ናት፤

ወደብረ ጽዮን ማዕከለ ሕንብርታ ለምድር፤

ቀራንዮም በምድር መካከል ያለች ናት፤

ወሠለስቲሆሙ፤

ገነት፤ ደብረ ሲና፤ ቀራንዮ እነዚህ ሶስቱ ሁሉ፤

ዝንቱ መንጸረ ዝንቱ ለቅድስት ተፈጥሩ፤

አንዱ በአንዱ አንጻር ለምስ ጋና ተፈጠሩ፤

፱፤ ወባረኮ ለአምላክ አማልክት፤

የካህናት ፈጣሪን አመሰገነው፤

ዘወደየ ውስተ አፉሁ ንባበ እግዚአ ብሔር እስከ ለዓለም፤

የእግዚአብሔር ምስጋና በአን ደበቱ ያደረበት ሰው ለዘለዓ ለሙ የካህናትን ፈጣሪ ለማ መስገን ተፈጠረ፤

ወአእመረ ከመ መክፈልተ በረከት ወቡራኬ በጽሐ ለሴም፤

በረከት ቡራኬ ያለው ዕጣ ሁሉ ለሴም እንደ ደረሰው አወቀ፤

ወውሉዱ ለትውልድ ዘለዓለም፤

ለዘለዓለም ጸንቶ ሊኖር ለል ጆቹ ለልጅ ልጆቹም እንደ ደረሰው አወቀ፤

፲፤ ኩላ ምድረ ኤዶም፤

የኤዶም አውራጃ ሁሉ፤

ወኩላ ምድረ ጽባሕ፤

የምሥራቁ አውራጃ ሁሉ፤

ወሕንደኬ፤

የሕንደኬ አውራጃ ሁሉ፤ ወበኤርትራ፤

በኤርትራ ያለው፤

ወአድባሪሁ፤

ተራራው፤

ወኩላ ምድረ ባሳን፤

የባሳን አውራጃ ሁሉ፤

ወኩላ ምድረ ሊባኖስ፤

የሊባኖስ አውራጃ ሁሉ፤

ወደስያተ ክፍቱር፤

ያልተገረዙ አሕዛብ ደሴት ሁሉ፤ አንድም በክፉ ቦታ የሚኖሩ አሕዛብ አውራጃ ሁሉ፤

ወኩሉ ደብረ ሳኔር፤

ሳኔር የሚባለው ተራራ ሁሉ፤

ወአማና፤

አማና የሚባለው ሀገር ሁሉ፤

ወደብረ አሡር ዘደቡብ፤

በደቡብ ያለ የአሡር አውራጃ ሁሉ፤

ወኵሉ ምድረ ኤላም፤

የኤላም አውራጃ ሁሉ፤

ወዐሡር ወባቢል፤

አሡር ባቢል የሚባለው፤

ወሱሳን፤

ሱሳን የሚባለው አገር፤

ወማዕዳይ፤

ማዕዳይ የሚባው ሀገር፤

ወኵሉ ምድረ አራራት፤

የአራራት አውራጃ ሁሉ፤

ወኵሉ ማዕዶተ ባሕር ዘማዕዶተ ደብረ አሡር፤

በአሡር ተራራ ማዶ ያለ የባሕሩ አውራጃ ሁሉ፤

ዘመንገለ ደቡብ ምድር፤

በደቡብ አውራጃ ያለው፤ ቡርክት ወስፍሕት፤

የሰፋች የከበረች በምትሆን በኢየሩሳሌም በኩል ያለች አውራጃ ሁሉ፤

ወኵሉ ዘውስቴታ ጥቀ ሠናይት፤

እጅግ ያማረው በሷ ውስጥ ያለው አውራጃ ሁሉ ለሴም ለልጆቹ እንደ ደረሰው አወቀ፤

፲፩፤ ወለካም ወጽአ መክፈልት ዘዳ ግም፤

ዳግመኛ የካም ዕጣ ወጣ፤

መንገለ ማዕዶተ ግዮን፤

የዓባይ አውራጃ ሁሉ፤

መንገለ ሰሜን በየማነ ገነት፤

በገነት ቀኝ በሰሜን በኩል ያለው፤

ወየሐውር መንገለ ሰሜን፤

ወደ ሰሜን ይደርሳል፤

ወየሐውር ኵሉ አድባረ እሳት፤

የእሳት ተራራ ከአለበት ይደር ሳል፤

ወየሐውር መንገለ ዓረብ መንገለ ባሕረ አጢል፤

በአጢል ባሕር በኩል እስከ ምዕራብ ይደርሳል፤

ወየሐውር ዓረበ እስከ ባሕረ አማ

ውክ፤

በመተማ እስከ አለው ባሕር ድረስ ክምዕራብ ይደርሳል፤

እንተ ይእቲ ዘኵሉ ይወርድ ውስ ቴታ ዘይትሐጐል፤

ይህችውም ወደሷ የሚኼድ ሰው ሁሉ የሚጠፋባት ናት፤

ወይመጽእ ውስተ ደቡብ ውስተ ጽንፈ ጋዲት፤

በደቡብ በኩል እስከ ጋዲት ድረስ፤

፲፪፤ ወይመጽእ ውስተ ክንፈረ ማየ ባሕር፤

ከባሕር እስከ አለው ውሀ ዳርቻ ይደርሳል፤

ውስተ ማያተ ባሕር ዓቢይ፤

በኤርትራ እስከ አለው ውሀ ድረስ፤

እስከ ሶበ ይቀርብ ፈለገ ግዮን ፣

እስከ ዓባይ ወንዝ አጠገብ ድረስ፤

፲፫፤ ወየሐውር ግዮን፤ፈለግ እስከ ሶበ ይቀርብ በይምነ ገነተ ኤዶም፤

ዓባይም ኤዶም በምትባል በገ ነት ቀኝ በኩል እስከሚደር ስበት ድረስ ይሔዳል፤

ወዛቲ ምድር እንተ ወጽአት ለካም፤

ለካም የደረሰችው ሀገር ይህች ናት፤

በመክፈልት ዘይእኅዝ ለዓለም ሎቱ ወለውሉዱ ለትዝምዶሙ እስከ ለዓ ለም፤

ለሱም ለልጆቹም ለወገኖቻ ቸው ጸንቶ ሊኖር በያዘው ዕጣ የደረሰው ይህ ነው፤

፲፫፤ ወለያፌት ወጽአ መክፈልት ሣልሳይ፤

ለያፌትም ሦስተኛ ዕጣ ወጣ ለት፣

ጢና በሚሰል ወንዝ ማዶ፣

መንገለ ደቡባቲሃ ለሙዳኅ ማያቲ ሆሙ፤

የውሀዎች መውጫ በምት ኸን በኩል ያለ፤

ወየሐውር መንገለ ጽባሕ ደቡብ ኵሉ ደወለ ጎግ፤

የጎግ አውራጃ ሁሉ እስከ

ደቡብ ምሥራቅ ይደርሳል።

ወኵሉ ዘጽባሐቲሆሙ።

በምሥራቅ ሀገር ያለው ሁሉ።

ወየሐውር መንገለ ደቡብ። ወደ ግራ ይደርሳል።

ወመንገለ ደቡብ ለደቡብ።

ከግራውም ወደ ግራ ይደር ሳል።

ወየሐውር አድባረ ቁልጥ መንገለ ደቡብ።

በደቡብ በኩል ቁልጥ እስከሚ ባለው ተራራ ይደርሳል።

ወመንገለ ባሕረ ማኡት።

በማኡት ከአለው ባሕር ጀምሮ።

ወይመጽእ መንገለ ጽባሑ ለጋ ዴር።

እስከ ጋዴር ምሥራቅ ይደር ሳል።

እስከ ውእደ ማየ ባሕር።

በባሕር እስከ አለው ውሀ ይደ ርሳል።

ወየሐውር እስከ ሶበ ይቀርብ መንገለ ዓረበ ፋራ።

ወደፋራ ምዕራብ እስኪደርስ ድረስ።

ወይገብእ መንገለ አፌራግ።

ወደአፌራግ ይመለሳል።

ወየሐውር መንገለ ጽባሕ መንገለ ማየ ባሕረ ሚአት።

ሚአት በሚባል ባሕር በኩል ወደምሥራቅ ይደርሳል።

ወየሐውር መንገለ ውእደ ጢና ፈለግ።

ጢና ከሚባል ወንዝ ይደር ሳል።

መንገለ ጽባሐ ደቡብ።

በደቡብ ምሥራቅ በኩል።

እስከ ሶበ ይቀርብ እስከ ጽንፈ ማያቲሆሙ።

ወደ ውሃቸው ዳርቻ እስኪ ደርስ ድረስ።

መንገለ ደብረ ራፋ።

እስከ ራፋ ተራራ ድረስ።

፲፬። ወየአውዳ ለደቡብ።

ደቡብን ይከባታል።

ዛቲ ምድር እንተ ወጽአት ለያ ፈት።

ለያፌት የወጣች ሀገር ይህች ናት፤

ወለውሉዱ በመክፈልተ ርስቱ ዘይ እኅዝ ለዓለም፣

ይዞት በሚኖር በዕጣ የደረ ሰው ይህ ነው፤

ሎቱ ወለውሉዱ ለትዝምዱ እስከ ለዓለም፤

ለሱ ለልጆቹ ለወገኖቹም ለዘ ለዓለም ጠንቶ ይኖር ዘንድ፤

ደለያት ዓበይት ሐምስቱ፤

ትልልቆቹ ሀገሮች አምስት ናቸው፤

ወምድር ዓባይ በደቡብ፤

በደቡብ ሰፊ ሀገር አለች፤

ወባሕቱ ቈራር ይእቲ ምድረ ያፌት፣

ነገር ግን የያፌት አገር ደጋ ናት፤

ወምድረ ካም መርቁ ይእቲ፣

የካም አገር ቆላ ናት፤

ወምድረ ሴምሰ ኢመርቁ ወኢደ ደክ፤
የሴም አገር ግን፤ ደጋም ቈላም አይደለችም መካከለኛ ናት፤

እስመ ቱስሕት ይእቲ በቍር ወበ ሞቅ፤

በሙቀትና በቅዝቃዜ የተቀላ ቀለች ናት፤

፲፩ ወከፈለ ካም ማእከለ ውሉዱ፤

ካምም በልጆቹ መካከል ምድርን ከፈለ፤

ወወጽአ መክፈልት ቀዳሚ ለኩሳ፣

በመጀመሪያው ለኩሳ ዕጣ ወጣ፣

መንገለ ጽባሕ፤

በምሥራቅ በኩል፤

ወዓረቢሃ ለሜጽራም

የሜጽራም ምዕራብ፤

ወዓረቢሁ ሎቱ ለፉድ፣

ምዕራቡ ለፉድ ደረሰ፤

ወዓረቢሁ ሎቱ ለከነአን፤

ምዕራቡም ለከነዓን ወጣ፤

ወመንገለ ዓረበ ባሕር፤

በባሕር በኩል ያለው ሁሉ ለእርሱ ደረሰ፤

፲፮፤ ወሴምኒ ከፈለ ውእቱኒ ማእ
ከለ ውሉዱ፤

ውእቱኒ ለካም ነው፤ ሴምም
በልጆቹ መካከል ከፈለ፤

ወወጽአ መክፈልት ቀዳሚ ለኤ
ላም፤

መጀመሪያ ለኤላም ዕጣ ወጣ
ለት፤

ወለውሉዱ መንገለ ጽባሕ ለጤግ
ሮስ፤

ጤግሮስ የሚባል ወንዝ ምሥ
ራቁ ለልጆቹ ደረሰ፤

እስከ ሶባ ይቀርብ መንገለ ጽባሕ
ምድር ኩላ፤

ወደሀገሩ፤

ሁሉ ምሥራቅ እስኪደርስ፤

ወምድረ ሕንደኬ፤

እስከ ሕንደኬ ድረስ፤

ወኤርትራ በእዴሁ፤

ኤርትራም በሱ እጅ ያለች
ናት፤

ወማያተ ዲዳን፤

የዲዳን ውሃ፤

ወኩሉ አድባር ዘምዕራብ፤

በምዕራብ ያለ ተራራ ሁሉ፤
ወኤላ፤

ኤላ በፋርስ ያለች ሀገር
ናት፤

ወኩሉ ምድረ ሱሳን፤

የሱሳን አውራጃ ሁሉ፤

ወኩሉ ዘበውእደ ፈርናክ፤

በፈርናክ ዘንድ ያለው ሀገር
ሁሉ፤

እስከ ባሕረ ኤርትራ፤

እስከ ኤርትራ ባሕር ድረስ፤

ወእስከ ጢና ፈለግ፤

ጢና እስከ ሚባለው ወንዝ
ድረስ፤

፲፯፤ ወለአሦር ወጽአ መክፈልት
ካልዕ፤

ለአሦርም ሁለተኛ ዕጣ ወጣ
ለት፤

ወኩሉ ምድረ ዐሡር፤

የዐሡር አውራጃ ሁሉ፤

ነነዌ ወሰናኦር፤

ነነዌ ሰናኦር ለሱ ደረሰ፤

ወላድ፤

ሳድም ለሱ ደረሰች፤

እስከ ቅሩብ ሕንደኬ፤

እስከ ሕንደኬ አጠገብ ድረስ፤

ወየዐርግ፤ ወጽፋ ፈለግ፣

ወደ ወጽፋ ፈሳሻም ይወ ጣል፤

፲፰፤ ወለአርፋስክድ ወጽአ መክፈ ልት ሣልስ፤

ለአርፋስክድም ሦስተኛ ዕጣ ወጣለት፤

ኵሉ ምድር ዘደወለ ከላውዴዎን፤

በከላውዴዎን አውራጃ ያለው ምድር ሁሉ፣

መንገለ ጽባሑ ለኤፍራጥስ ዘቅሩብ ለባሕረ ኤርትራ፤

የኤርትራ ባሕር አቅራቢያ የሚሆን የኤፍራጥስ ምሥ ራቁ ሁሉ፤

ወኵሉ ማያተ ገዳም፤

በምድረ በዳ ያለው ውሀ ሁሉ፤

እስከ ቅሩብ ውስተ ልሳነ ባሕር፤

እስከ ልሳነ ባሕር (ባሕረ ሰላጤ) አጠገብ ድረስ፤

እንተ ትኔጽር መንገለ ግብፅ፤

በግብፅ አንፃር ያለች፤

ኵላ ምድረ ሊባናስ፣

የደጋው አውራጃ ሁሉ፤

ወሳኔር ወአማና እስከ ቅሩብ ኤው ፍራጢስ፤

የሳኔርና የደጋው አገር አማ ናም እስከ ኤውፍራጢስ አው ራጃ ድረስ፤ እነዚህ ሁሉ የአርፋስክድ ዕጣዎች ናቸው፤

፲፱፤ ወለአራም ወጽአ መክፈልት ራብዕ፣

ለአራምም ዓራተኛ ዕጣ ወጣ ለት፤

ኵላ ምድረ መስጴጦምያ ማዕከለ ጤግሮስ ወኤውፍራጢስ፣

በኤውፍራጢስና በጤግሮስ መካከል ያለ የመስጴጦምያ አውራጃ ሁሉ፣

ወመንገለ ደቡብ ከለዳውያን፤

በከለውዴዎን ደቡብ በኩል፣

እስከ ቅሩብ ደብረ ዐሡር፤

እስከ ዐሡር አጠገብ ተራራ ድረስ፣

ወምድረ አራራት፤

የአራራትም ሀገር ሁሉ እነ ዚህ ሁሉ የአራም ዕጣ ናቸው፤

፳፤ ወለሉድ ወጽአ መክፈልት ሐምስ፤

ለሉድም አምስተኛ ዕጣ ወጣ ለት፤

ደብረ ዐሠር፤

ዐሠር የሚባል ተራራ፤

ወኩሉ ዘዚአሁ፤

የሱን አውራጃ ሁሉ፤

እስከ ይቀርብ ባሕረ ዓቢየ፤

እስከ ኢያሪኮ ድረስ፤

ወይቀርብ መንገለ ጽባሕ ዐሥር እጉሁ፤

ወደወንድሙ ወደ ዐሥር ዕጣ ይደርሳል፤

፳፩፤ ወያፈት ውእቱኒ ከፈለ ምድረ ርስት ማዕከለ ውሉዱ፤

ያፈትም ርስት ሊሆነው ምድሩን በልጆቹ መካከል ከፈለ፤

ወወጽአ መክፈልት ቀዳሚ ለሴሜር፤

መጀመሪያ ዕጣ ለሴሜር ወጣ፤

መንገለ ጽባሕ እምገጸ ደቡብ እስከ ጢና ፈለግ፤

በደቡብ አንባር በምሥራቅ በኩል ጢና እስከሚባለው ወንዝ ድረስ ወጣ፤

ወደቡብ ለማጎግ፤

በደቡብ በኩል ለማጎግ ደረሰ፤

ወጽአ ኩሉ ውሳጥያቲሁ ለደቡብ፤

የደቡብ ቆላ ሁሉ፤

እስከ ይቀርብ መንገለ ባሕረ ሜአት፤

እስከ ባሕረ ሜአት ድረስ ለማጎግ ወጣ።

፳፪፤ ወለማዳይ ወጽአ መክፈልት፤

ለማዳይም ዕጣ ወጣለት፤

ከመ የአኃዝ እምዓረብ ለክልኤ ሆሙ አኃዊሁ፤

ለሁለቱ ወንድሞቹ ሁሉ ከምዕራብ ጀምሮ እስከ ደሴቶቹ ድረስ ይይዝ ዘንድ፤

ወእስከ ጽነፈሆን ለደሰያት፤

እስከ ደሴቶቹም ዳርቻ ድረስ ለማዳይ ሆነ፤

፳፫፤ ወለኢዮእያን ወጽአ መክፈልት ራብዕ፤

ዐራተኛ ዕጣ ለኢዮእያን ወጣ፤

ኵሉ ደሴት ወደሰያት ዘመንገለ እደ ሉድ፤

በሱ እጅ ያሉ ደሴቶች ሁሉ እነዚህ ናቸው፤

፳፬፤ ወለቶቤልሂ ወጽአ መክፈልት ሐምስ፤

ለቶቤልም አምስተኛ ዕጣ ወጣለት፤

ማዕከለ ልሳን እንተ ትቀርብ መን ገለ ውሉደ መክፈልተ ሉድ፤

ወደሉድ ዕጣ እስከ እምትቀርብ በልሳን መካከል ወጣ፤

እስከ ልሳን ካልእት፤

እስከ ሁለተኛይቱ ልሳን ድረስ፤

ወማዕዶታ ለልሳን ካልእት፤

የሁለተኛይቱ ልሳን ማዶ፤

ውስተ ልሳን ሣልሲት፤

እስከ ሶስተኛይቱ ልሳን ድረስ ነው፤

፳፭፤ ወለሞሳክ ወጽአ መክፈልት ሳድስ፤

ለሞሳክም ስድስተኛው ዕጣ ወጣለት፤

ወኵሉ ማዕዶተ ልሳን ዘሣልስት፤

የሶስተኛይቱም ልሳን ማዶ ሁሉ፤

እስከ ይቀርብ ጽባሒሁ ለጋዴር፤

እስከ ጋዴር ምሥራቅ ድረስ ወጣለት፤

፳፮፤ ወለቲራስ ወጽአ መክፈልት ሳብዕ፤

ለቲራስም ሰባተኛ ዕጣ ወጣለት፤

አርባዕቱ ደሰያት ዓበይት በማዕከለ ባሕር እለ ይቀርባ ለመክፈልተ ካም፤

ለካም ዕጣ አቅራቢያ የሚሆኑ አራት ትልልቆች ደሴቶች ናቸው፤

ወደሰያት ዘከማቱሪ፤

በከማቱሪ ያሉ ደሴቶች፤

ለውሉደ፤ አርፋስክድ ወጽአ በዐ ዋዊ ርስቱ ሎቱ፤

ለሱ ርስት ሊሆነው በዕጣ ለአርፋስክድ ልጆች ወጣ፤

ወከፈሉ ከመዝ ደቂቀ ኖኅ ለደቂቆሙ በቅድመ ኖኅ አቡሆሙ፤

የኖኅ ልጆች በአባታቸው ኖኅ ፊት ለልጆቻቸው እንዲህ አድርገው ከፈሉ፤

ወአምሐለ በመርገም፤

በርግማን አማለ፤

ወረገሞ ለኵሉ በበፅፅዱ ዘፈቀደ የአኃዝ መክፈልተ ዘኢወጽአ በአፃዌሁ፤

በዕጣ ያልደረሰውን ይይዝ ዘንድ የወደደውን አንዱንም፤ አንዱንም ሁሉ አምሎ ረገመ፤

፳፯፤ ወይቤሉ ኵሎሙ ለይኩን ለይኩን፤

ሁሉም ይሁን ይሁን አሉ፤

ሎሙ ወለውሉዶሙ እስከ ለዓለም ለትዝምዶሙ፤

በዘመናቸው ለዘላለሙ፤ በራሳቸውም በልጆቻቸውም ይሁን ይደረግ አሉ፤

እስከ አመ ዕለተ ደይን በዘይኴን ኖሙ እግዚአብሔር አምላኮሙ በሰይፍ ወበእሳት፤

ፈጣሪያአቸው የሚሆን እግዚአብሔር በሰይፍ በእሳት በሚ ፈርድባቸው ገንዘብ ቁርጥ ፍርድ እስከ ሚያደርግባት ቀን ድረስ፤

በእንተ ኵሉ እዙይ ዘርዙስ ጌጋ ዮሙ፤

በደል፤ ኃጢአት ስለሚሆን ክፉ ሥራቸው፤

ዘመልዕዋ ለምድር አበሳ ወዝሙተ ወርዙሰ ወኃጢአተ፤

ምድርን ኃጢአትን በደልን ዝሙትን በሚያፀይፍ ክፉ ሥራ ስለ ሞሏት ይሁን ይሁን አሉ።

ምዕራፍ ፲

፩፤ ወበሱባዔ ሣልስ ዘኢዮቤልዩ ዝንቱ፤

በዚህ ኢዮቤልዩ በሶስተኛው ሱባዔ፤

አኀዙ አጋንንት ርኩሳን ያስሕት ሙ ለደቂቀ ውሉደ ኖኅ፤

የኖኅን የልጅ ልጆች አጋንንት ያስቷቸው ጀመር፤

ወያአብድሙ ወያኃጕልሙ፤

አእምሮአቸውን ያሳጧቸውይጎዷቸው ጀመር፤

፪፤ መጽኡ ውሉደ ኖኅ ኀበ ኖኅ አቡሆሙ፤

የኖኅ ልጆች ወደ አባታቸው ኖኅ ዘንድ መጥተው፤

ወነገርዎ በእንተ አጋንንት እለ ያስሕቱ፤

የሚያስቱ የአጋንንትን ነገር ነገሩት፤

ወይጼልሉ፤

አእምሮ የሚያሳጡ የሚያደነቁሩ፤

ወይቀትሉ ውሉደ ውሉዱ፤

የልጅ ልጆቹን የሚጎዱ የአጋንንትን ነገር ነገሩት፤

፫፤ ወጸለየ ኖኅ ቅድመ እግዚአብሔር አምላኩ፤

ኖኅም በፈጣሪው እግዚአብሔር ፊት ለመነ፤

ወይቤ አምላከ መናፍስት ዘውስተ ኵሉ ዘሥጋ፤

በሥጋዊ በደማዊ ያለ ሁሉ የነፍሳት ፈጣሪ፤

ዘገበርከ ምሕረተከ፤

ይቅርታህን ያደረግህ፤

ወአድኃንከኒ፤

እኔን ያዳንክኸኝ፤

ወውሉድየኒ እምነ ማያተ አይኅ፤

ልጆቼንም ከማየ አይኅ፤ ከጥፋት ውሀ ያደንካቸው፤

ወኢገበርከኒ ከመ እኅልቅ፤

እንድጠፋም ያላደረግኸኝ፤

በከመ ገበርከ ለወልደ ኃጕል፤

ጥፋት የሚገባው ቃየልን እንዳጠፋኸው እንድጠፋ ያለደረግኸኝ አቤቱ፤

እስመ ዓቢይ ሣህልከ ላዕሌየ፤

በኔ ላይ ይቅርታህ ብዙ ነውና፤

ወዓብየት ምሕረትከ ላዕሌየ፤

ቸርነትህ በኔ ላይ በዝታለችና፤

ወይትሰዓል ሣህልከ ላዕለ ውሉድየ፤

ይቅርታህ በእኔና በልጆቼ ላይ ይብዛ ከፍ ከፍ ይበል ብሎ ጸለየ፤

ወኢይመብሉ መናፍስት፤ እኩያን ላዕሌሆሙ፤

እኩያን አጋንንት በነዚያ ላይ እንዳይሰለጥኑባቸው፤

ከመ ኢያማስንዎሙ እምነ ምድር፤

ከዚህ ዓለም እንዳያጠፏቸው በላያቸው አይሠልጥኑ አለ፤

፬፤ ወአንተኒ ባርከኒ ኪያየ ወውሉድየ፤

አንተ ግን እኔንም ልጆቼንም አክብር፤

ንልሐቅ ወንብዛኅ ወንምልዓ ለምድር፤

በዝተን ይህችን ዓለም እንመላት ዘንድ፤

ወአንተ ተአምር ዘከመ ገብሩ ትጉሃኒከ፤

ለምስጋና ለምግባር ይተጉ የነበሩ ደቂቀ ሴት፤

አበዊሆሙ ለእሉ መናፍስት፤

የሊህ የደቂቀ ሴት ልጆች አባቶቻቸው በዘመኔ ያደረጉትን አንተ ታውቃለህ፤

ለእሉ መናፍስት አለ ሀለዉ፤ በሕይወት ዕፀዎመ፡ ወአኃዞሙ ውስተ መካነ ደይን፤

በሕይወት ያሉ እሊህን መናፍስት ይዘህ ጽኑ መከራ በአ

ለበት መቻያ በሚደረግባት በገሃነም አስረህ አግዛቸው፤

ወኢያማስኑ ውሉደ ገብርከ አምላኪየ፤

ፈጣሪየ የኔን የባሪያህን ልጆች እንዳይጎዷቸው፤

እስመ ፀዋጋን እሙንቱ፤

እነሳቸው ክፉዎች ናቸውና፤

ወለአማስኖ ተፈጥሩ፤

ለማጥፋት ተፈጥረዋልና፤

መፈጠራቸውስ ለበጎ ነበር ፈጣሪያቸውን ከበደሉና ከካዱ በኋላ ሰውን ሁሉ የሚጎዱ የሚያጠፉ ሆነዋልና፤ ስለሆኑ እንዲህ አለ እንጂ፤

ወኢይመብሉ በመንፈሰ ሕያዋን፤

በሕይወት በሚኖሩ በሕያዋን ባሕርይ እንዳይሰለጥኑ፤

እስመ አንተ ተአምር ባሕቲትከ ዘነኔሆሙ፤

የነዚህን ፍርዳቸውን አንተ ብቻ ታውቃለህና፤

ወኢይተበውሑ ላዕለ ውሉደ ጻድቃን እምይእዜ ወእስከ ለዓለም፤

ከዛሬ ጀምሮ ለዘለዓለሙ በጻድቃን ልጆች ላይ እንዳይሰለ

ጥኑ ።

፮ ። ወይቤለነ አምላክነ ከመ ንእስር ኵሎ ።

አዘዘነ ሲል ነው እግዚአብ ሔር ሁሉን አሥረን እናግዝ ዘንድ አዘዘን ።

ወመጽአ መልአከ መናፍስት መስ ቴማ ።

መስቴማ ማለት መስተዋድይ ማለት ነው ሰውን ከሰው የሚ ያአጣላ የአጋንንት አለቃ ሰይ ጣን መጣ ።

ወይቤ እግዚኦ እግዚአብሔር ፈጣሪ አትርፍ እምኔሆሙ ቅድ ሜየ ።

አቤቱ ፈጣሪ እግዚእብሔር ከነሱ በፊት አጋንንትን ከጥ ፋት አስቀር አለኝ ።

ወይስምዑ ቃልየ ።

ነገሬን ይሰሙ ዘንድ ።

ወይግበሩ ኵሎ ዘእቤሎሙ ።

ያዘዝኋቸውን ሁሉ ያደርጉ ዘንድ ።

እስመ ለእመ ኢተርፉ ሊተ እምው ስቴቶሙ ኢይክል ገቢረ ሥልጣነ ፈቃድየ ውስተ ውሉደ ሰብእ

ፈቃደ ሥልጣንየ ሲል ነው ከነዚህ ካልቀሩልኝ በሰዎች ልጆች ዘንድ ፈቃዴ የምትፈ ጸምበትን ሥልጣን ማድረግ አልችልምና ።

እስመ እሙንቱ ውእቶሙ ለአ ማስኖ ወለአስሕቶ ቅድመ ኵነኔየ ።

እነዚህ በኔ ትእዘዝ ሰውን ለማሳት ሰውን ለመጉዳት ይላ ካሉና ።

፯ ። እስመ ዓቢይ እኮሙ ሰው ሉደ ሰብእ ።

የሰዎች ልጆች ክፋታቸው ብዙ ስለሆነ ።

ወይቤ ይትርፉ ቅድሜሁ አሥራቲ ሆሙ ።

በፊቱ ዓሥረኛው ነገድ ይቅሩ አለ ።

ወፀተ መክፈልተ ያውርዱ ውስተ መካነ ደይን ።

ዘጠኙን ነገድ ግን አጋንንት አሥረው መቻያ (ፅኑዕ መከራ) ወደአለበት ቦታ ወደ ገሃነም ያውርዷቸው አለ ።

ወለ፩ዱ እምኔነ ይቤ ከመ ንምሐሮ ለኖኅ ኵሎ ፈውሶሙ፤

ጌታ ለኛ ለአንዱ እንዲህ አለ መድኀኒታቸውን ሁሉ ለኖኅ እናስተምረው ዘንድ፣

እስመ የአምር ከመ አኮ በርትዕ ዘየሐውሩ፤

አጋንንት በጸና ሕግ ጸንተው እንደማይኖሩ ያውቃልና፤

ወአኮ በጽድቅ ዘይትበአሱ፤

የሚጣሉ በውነት እንዳይደለ ያውቃልና፤

፯፤ ወገበርነ በከመ ቃሉ ኵሎ እኩያነ እለ ይፀወጉ አሰርነ ውስተ መካነ ደይን፤

እሱ እንዳዘዘን አጋንንትን አስረን አጋዝናቸው፤

ወዓሥራቶሙ አትረፍነ፤ ከመይኰንኑ ቅድመ ሰይጣን ዲበ ምድር፤

በዚህ ዓለም በሰይጣን ፈቃድ ያስቱ ዘንድ አስረኛቸውን ነገድ ግን በሰይጣን ትእዛዝ በዚህ ዓለም መቻያ ይሆኑ ዘንድ አስቀረን፣

ወፈውሰ ደውዌሆሙ ኵሎ ነገርናሁ ለኖኅ ምስለ አስሕቶቶሙ፣

ከማሳታቸው ጋራ ያመጡትን ደዌ የሚያድንበትን ሁሉ ለኖኅ ነገርነው፣

ከመ ይፈውስ በዕፀወ ምድር፤

ከምድር በተገኘ እንጨት ያድን ዘንድ፣ ሺ ዕፀው ነግረ ውታል ሦስት መቶውን ቃል በቃል ነግረውታል ሰባት መቶ ውን ከቅቤ ከማር ታገኘዋለህ ብለውታል፣

፰፤ ወጸሐፈ ኖኅ ኵሎ ዘከመ መሐርናሁ በመጽሐፍ፤

ኖኅ እንዳስተማርነው በመጽ ሐፍ ጻፈው፤

በኵሉ ትዝምደ ፈውስ፤

የመድኃኒትን ወገን ሁሉ ጻፈ፣

ወተአፅዉ መናፍስት እኩያን እም ድኅሬሆሙ ለደቂቀ ኖኅ፤

አጋንንት የኖኅን ልጆች ከመ ከተል ተዘጉ ተከለከሉ፣

፱፤ ወወሀበ ኵሎ መጻሕፍተ ዘጸሐፈ ለሴም ወልዱ ዘይልህቅ፤

የጻፈውን መጽሐፍ ሁሉ ከሁሉ ለሚበልጥ ለልጁ ለሴም ሰጠው፤

እስመ ኪያሁ ያፈቅር ፈድፋደ እምኵሉ ውሉዱ፤

ከልጆቹ ሁሉ እሱን ፈጽሞ ይወድ ነበርና፤

ጉባኤ

ወኖመ ኖኅ ምስለ አበዊሁ፤

ኖኅ እንደአባቶቹ ከአባቶቹ ጋር አረፈ፤ (ሞተ)፤

ወተቀብረ ውስተ ሉባር ደብር በምድረ አራራት፤

በአራራት ምድረ በዳ ባለ ሉባር በሚባል ተራራ ተቀበረ፤

፱፻፸ተ ወ፱ ዓመተ ፈጸመ በሕይወቱ፤

ዘጠኝ መቶ ሃምሳውን ዘመን በሕይወቱ ፈጸመ፤

፲ወ፱ቱ ኢዮብልዩ ወ፱ቱ ሉባኤ ወ፭ቱ ዓመት፤

ይኸውም ዓሥራ ዘጠኝ ኢዮቤልዩ ከሁለት ሉባኤ ከአምስት ዘመን ነው፤ አንድም ዓሥራ ሁለት ኢዮቤልዩ ይሆናል፤

ዘአፈድፈደ ሐዲወ ዲበ ምድር እምውሉደ፣ ሰብአ

በዚህ ዓለም ከሰው በልጦ የኖረው ዘመን አምስት ዓመት ከሁለት ሉባዔ አሥራ ዘጠኝ ኢዮቤልዩ ነው፤

በእንተ ጽድቁ ዘባቲ ፍጹም በጽድቁ ዘአንበለ ሄኖክ፤

ከሄኖክ በቀር ከሰው ልጆች በዚህ ዓለም ዘመንን ያበዛ የለም ፤ በምግባር በትሩፋት ፍጹም ስለሆነ፤

እስመ ግብሩ ለሄኖክ ፍጥረት ውእቱ ለስምዕ ለትዝምደ ዓለም፤

ሄኖክ መፈጠሩ አምልኩቱን ለሰው ለማስተማር ለምስክርነት ነውና፤

ከመ ይንግር ኵሉ ግብረ ለትውልደ ትውልድ፤

ለዕለተ ደይን ቁርጥ ፍርድ በሚደረግባት ቀን ለልጅ ልጅ ሁሉ ሥራውን ይነግር ዘንድ፤

፲ ወበ፴ወ፫ኢዮቤልዩ በዓመት ፩ዱ በሉባዔ ካልዕ ነሥአ ሎቱ ፋሌክ ብእሲተ፤

በሠላሳ ሶስተኛው ኢዮቤልዩ በአንደኛው ዓመት፤ በሁለተ

ኛው ሱባዔ ፋሌክ ሚስትን አገባ፤

እንተ ስማ ሎምና፤

ስሟ ሎምና የምትባል፤

ወለተ ሲናኦር፣

የሲናኦር ልጅ ናት፣

ወወለደት ሎቱ ወልደ በዓመት፤ ራብዕ ዘሱባዔ ዝንቱ፣

በዚህ ሱባዔ ባራተኛው ዘመን ወንድ ልጅን ወለደችለት፤

ወጸውአ ስሞ ራግው፤

ስሙን ራግው አለው፤ ራግው ማለት ጽሩዕ እኩይ ማለት ነው፤

ከዚህ አስቀድሞ ሺህ ከ፭፻፷፯ ዘመን ይሆናል፤ ቢያገናኙት ሺህ ፯፻፳፰ ይሆናል ሺህ ፯፻ው ዘመን ፴ ኢዮቤልዩ ሁኖ ፴፪ ዘመን ይተርፋል፤ ፴፪ንና ፳፰ን ቢያገናኙት ፷ይሆናል፣ ፷ው አንድ ኢዮ ቤልዩ ሆኖ ፲፩ ዘመን ይተርፋል፤ በ፴፬ኛው ኢዮቤልዩ በ፪ኛው ሱባኤ በአ ራተኛው ዘመን ባለ በቀና ነበር፣ ኢዮቤልዩን አጎደለ፤

እስመ ይቤ ናሁ ውሉደ ሰብእ ኮኑ እኩያነ በምክረ ጹግ፤

በክፉ ምክር የቃየል ልጆች ክፉዎች ሁነዋልና ስሙን ራግው አለው፤

ከመ ይሕንጹ ሎሙ ሀገረ ወማኅፈደ ውስተ ምድረ ሰናኦር፤

ሰናኦር በምትባል ሀገር ቅጽ ሩን ግንቡን ይሠሩ ዘንድ፣

እስመ ፈለሱ እምድረ ዓራራት መንገለ ጽባሕ ውስተ ሰናዖር፣

ከአራራት ተነሥተው በምሥ ራቅ በኩል ወደሰናዖር ሄደዋ ልና፤

እስመ በመዋዕሊሁ ለራግው ሐነ ፅዋ ለሀገር ወለማኅፈድ ፣

በዘመኑ ቅጽሩን ግንቡን ሠር ተዋልና፤

እንዘ ይብሉ ቦቱ ነዐርግ ውስተ ሰማይ ወአኃዙ ይሕንጹ፤

ወደ ሰማይ እንወጣበታለን ብለው ይሠሩ ጀመሩ፤

፲፩፤ ወበሱባዔ ራብዕ ወፈጡ በእ ሳት፣

አውአዩ ሲል ነው፤ ባራተኛው ሱባዔ ጡቡን ሠርተው በእ

ሳት ተከሥ፤

ወኮኖሙ ግንፋል ከመ ዕብን፤

ጡቡም እንደ ድንጋይ ሆነላ ቸው፤

ወዕቡር በዘይመርጉ ቦቱ አስፈሲ ጦስ ዘይወጽእ እምነ ባሕር ወእ ምነ አንቅዕተ ማያት በምድረ ሰና ዖር፤

ኖራውን የሚመርጉበት ጭቃው በሰናኦር ምድር ካሉ ከምንጮችና ከባሕር የሚገኝ የባሕር አረፋ ሆነላቸው፤

፲፪፤ ወሐነጽዎ ፸ወ፫ተ ዓመተ፤

አርባ ሦስት ዓመት ሠሩት፤ ወሀለዉ ዝየ እንዘ የሐንጽዎ ግን ፋለ ፍጹመ ፫ቱ ወ ፲ውስቴቱ፤

ፍጹም ጡብ አድርገው ሲሠ ሩት ኖሩ በጡቡ ሦስት ነገር አለበት፤

አቆልቋዩ ዓሥር ክንድ ነው፤

ወ፫ቱ አሐቲ ለኵት፤

ቁመቱና ወርዱ አንድ ወገን ነው፤ ቁመቱ ሦስት፤ ወር ዱም ሦስት ክንድ ነው፤

ሐምሳ ምዕት ወአርባዕቱ ምዕት ወሠላሳ ወሠላስ በእመት ዓርገ ኑት ወክልኤቱ ስዝር፤

ወደላይ ቁመቱ አምስት ሽሕ ከአራት መቶ ሠላሳ ሶስት ክንድ ከሁለት ስንዝር ወደ ሰማይ ወጣ፤

፲፩ቱ ወ፫ምዕራፍ፤

የተሠራበት ምዕራፍ ዐስራ ሶስት አቄልቋይ ነው፤ አንዳ ንዱ ምዕራፍ ማለት የወን ድና የሴት አካሄድ የሚለይ በት የሚታወቅበት ነው፤ አን ድም ስልሳ ገመል ከነሳቢው ከነመሳብያው አተርትሮ የሚ አቆምበት፤ የፈረስ አፍታ የሚ ያድክም ጕልማሳ ፍላፃ ወር ውሮ የሚያደርስበት ነው።

፲፫፤ ወይቤለነ እግዚአብሔር አም ላክነ ለነ፤

አዘዘነ ሲል ነው፤ ፈጣሪአችን እግዚአብሔር እኛን እንዲህ አለን፤

ናሁ ሕዝብ ፩ዱ፤

እነሆ ይህ ወገን በአንድ ቋንቋ ይናገራል፤

ወወጠነ ይግበር፤

ግንብ ይሠራ ጀመር፤

ወይእዜኒ ኢናኀልቅ እምኔሆሙ ንዑ ንረድ ወንከፀው ልሳናቲሆሙ፤

አሁንም ከነሳቸው ፈጽመን እናጥፋ ወርደን በቦታ በቋንቋ እንለያያቸው፤

ወኢይስማዕ ፩ዱ ቃለ ካልኡ ወይዘ ረዉ ውስተ አህጉር፤

በየሐገሩ አንዱ ያንዱን ቋንቋ እንዳይሰማ፤

ወውስተ አሕዛብ፤

በአሕዛም ዘንድ እንዳይሰማ በየሀገሩ ይበተኑ፤

ወኢትንበር እንከ አሐቲ ምክር ላዕሌሆሙ፤

አንዲት ቋንቋ በነዚያ ላይ ጸንታ እንዳትኖር፤

እስከ አመ ዕለተ ደይን፤

ቁርጥ ፍርድ እስከ ሚደረግ በት ቀን ድረስ ጸንታ አትኑር አለን አሉ፤

፲፬፤ ወወረደ እግዚአብሔር፤

እግዚአብሔር በግብር ወረደ፤

ወወረድነ ምስሌሁ ንርአይ ሀገረ ወማኅፈደ ዘሐነጹ ውሉደ ሰብእ፤

የሰዎች ልጆች የሠሩትን ግን ቡንና ከተማውን እናይ ዘንድ፤ እኛም ከሱ ጋራ ወረድን፤

ወሥጠ ኵሎ ቃለ ልሳናቲሆሙ፤

አንድ ቋንቋ የነበሩ ሰባ ሁለት ቋንቋ ቀላቀለባቸው፤

ወኢሰምዐ እንከ አሐዱ ቃለ ካልኡ፤

ከዚህ በኋላ አንዱ ያንዱን ቃል አልሰማም፤

ወአንተጉ እንከ ሐኒጸ ሀገር ወማ ህፈድ፤

ድንጊያ ስጠኝ ሲለው ጭቃ፤ ጭቃ ስጠኝ ሲለው ድንጊያ አያመጣ ግንቡን ቅጽሩን መሥ ራት ተዉ፤

፲፭፤ ወበእንተዝ ተሰምየት ኵላ ምድረ ሰናኦር ባቢል፤

ስለዚህ ነገር የሰናኦር አው ራጃ ሁሉ ዝሩት ተባለች፤

እስመ በህየ ሦጠ አምላክ ኵሎ ልሳናቲሆሙ ለውሉደ ሰብእ፤

አምላክ ፈጣሪ በዝያ የሰዎ ችን ቋንቋቸውን ለውጧልና፤ አንድም ሦጠ ያለውን ወለጠ ይላል፤

ወእምህየ ተዘርዉ ውስተ አህጉሪ ሆሙ በበልሳናቲሆሙ ወበበሕዘቢ ሆሙ፤

ከዝያ በየወገናቸው በየቋንቋ ቸው ወደሀገራቸው ተበተኑ።

፲፮። ወፈነወ እግዚአብሔር ነፋሰ ዓቢየ ውስተ ማኅፈዶሙ፣

እግዚአብሔር በግንባቸው ላይ ጽኑዕ ነፋስን አመጣ።

ወገፍትአ ውስተ ምድር፣ ገፍቶ ግንቡን ከምድር ጣለው ገለበ ጠው።

ወናሁ ውእቱ ማዕከለ አሶር ወባቢ ሎን ውስተ ምድረ ሰናኦር።

እነሆ ይህ በአሦርና በባቢሎን መካከል በሰናኦር አውራጃ ነው።

ወጸውአ ስማ ድቀት።

ስሟንም መከራ አላት።

በሱባዔ ራብዕ በ፩ዓመት በቅድመ ዚአሁ ዘ ፴ወ፬ ኢዮቤልዩ፣

ዚአሁ ለዓመት ነው ባራተኛው ሱባዔ በአንድ ዓመት በሠላሳ አራተኛው ኢዮቤልዩ።

ተዘርዉ እምድረ ሰናኦር፣

በሱ ትእዛዝ ከሰናኦር ሀገር ተበተኑ።

፲፯። ወሖሩ ካም ወወሎዱ ውስተ ምድር እንተ አኅዝት ሎቱ ዘረከበ ሎቱ በመክፈልት ውስተ ምድረ ደቡብ።

ካምና ልጆቹ ከሥራው ነበሩ ና በዕጣ ወደደረሰችው ይዟ ቸው ወደሚኖር ሀገር ደቡብ ሔዱ።

ወርእየ ከነአን ምድረ ሊባኖስ እስከ ሙሐዘ ግብፅ፣

ከደጋው ጀምሮ እስከ ግብጽ አውራጃ ድረስ ከነአን የሴምን ዕጣ አየ።

ከመ ሠናይት ይእቲ ጥቀ።

እርሷ እጅግ የአማረች እነደ ሆነች አየ፣

ወኢሖረ ውስተ ምድረ ርስቱ መን ገለ ዓረበ ባሕር፣

በምዕራብ በኩል ወደአለ ወደ ርስቱ አውራጃ አልሄደም።

ወኀደረ ውስተ ምድረ ሊባኖስ እምጽባሕ ወእስከ ዓረብ።

ከምሥራቅ ጀምሮ እስከ ምዕ ራብ ድረስ በሴም ዕጣ ኖረ።

እምውዕደ ሊባኖስ ወበውዕደ ባሕር፣

በባሕሩና በደጋው ዙሪያ ኖረ።

፲፰፤ ወይቤሎ ካም አቡሁ፤

አባቱ ካም፤

ወኩሳ ወመጽሪም አኀዊሁ፤

ወንድሞቹም ኩሳና መጽሬም እንዲህ አሉት፤

እስመ ኀደርከ ውስተ ምድር እንተ ኢኮነት እንቲአከ፤

ገንዘብህ ባይደለች ሀገር ኑረሃልና፤

ወኢወጽአት ለነ በዕፃ፤

በዕጣ ለኛ አልወጣችልንምና፤

ኢትግበር ከመዝ፤

እንዲህ አታድርግ፤

እስመ ለእመ ከመዝ ገበርከ አንተሂ ወደቂቅከ ትወድቁ ውስተ ምድር፤

እንዲህ ብታርግ አንተም ልጆችህም ከዚህ ዓለም ትጠፋላችሁ፤

ወርጉማን በሐከክ፤

በጸብ በክርክር ርጉማን ትሆናላችሁ፤

እስመ በሐከክ ኀደርከሙ፤

በጸብ በመከራከር ኑራችኁ ልና፤

ወበሐከክ ይወድቁ ደቂቅከ፤

ልጆችህም በፀብ በመከራ ይጠፋሉ፤

ወትሜሮ ለዓለም፤

አንተ ለዘለዓለም ትጠፋለህ፤

፲፱፤ ወኢትኀድር ውስተ ማኀደሩ ለሴም፤

በሴም ዕጣ አትኑር፤

እስመ ለሴም ወለውሉዱ ወጽአ በዕፃሆሙ፤

ለልጆቹና ለሴም በዕጣቸው ወጥቶላቸዋልና፤

ርጉም አንተ፤

አንተ ርጉም ነህ፤

ወርጉመ ትከውን እምኵሉሙ ደቂቀ ኖኅ፤

ከኖኅ ልጆች ሁሉ ተለይተህ አንተ ርጉም ትሆናለህ፤

ለመርገም እንተ ሠራዕነ፤

በመሐላ በቅዳሜሁ ለመኰንን ቅዱስ፤

በመልአከ ገጹ ፊት በመሐላ በሠራነው መርገም፤

ወበቅድመ ኖኅ አቡነ።

በአባታችን ኖኅ ፊት ርጉም ትሆናለህ አሉት።

ወኢሰምዖሙ።

አልሰማቸውም።

ወኀደረ ውስተ ምድረ ሊባናስ እምኤማት እስከ መባአ ግብጽ።

ከኤማት ጀምሮ እስከ ግብጽ መግቢያ ድረስ በሴም ዕጣ ኖረ።

ውእቱ ወውሉዱ እስከ ዛቲ ዕለት።

ሲጽፍ እንዲህ አለ እሱም ልጆቹም እስከ ዛሬ ድረስ በሴም ዕጣ ኖሩ።

ወበእንተ ዝንቱ ተሰምየት ይእቲ ምድረ ከነአን።

ስለዚህ ነገር የሴም ዕጣ የከነዓን አገር ተባለች።

፳። ወያፌትሰ ወውሉዱ ሖሩ መንገለ ባሕር ።

ያፌትና ልጆቹ ግን ወደ ምዕራብ ሄዱ።

ወኀደሩ ውስተ ምድረ መክፈል ቶሙ።

በዕጣቸው ሀገር ኖሩ።

፳፩። ወርእየ ማዳይ ምድረ ባሕር።

ማዳይ በምዕራብ በኩል ያለውን ውሃ ያለበትን አገር አየ።

ወኢአደመቶ በቅድሜሁ።

ነገር ግን በፊቱ ደስ አላሰኘችውም።

ወአስተብቍዐ እምኀበ ኤላም ወአሡር ወአርፋስክድ እምኀበ እኀዉ ብእሲቱ።

ከሚስቱ ወንድሞች ከአርፋስክድ ከአሡር ከኤላም ዘንድ ለመነ።

ወኀደረ ውስተ ምድረ መቄዶን ቅሩበ ኀበ እኀዉ ብእሲቱ እስከ ዛቲ ዕለት።

እስከዚች ቀን ድረስ በሚስቱ ወንድሞች አገር አቅራቢያ በምትሆን በመቄዶን ኖረ።

ወሰመየ ምንባሪሁ።

እሱ የሚኖርበትን።

ወምንባረ ውሉዱ።

ልጆቹ የሚኖሩበትን ቦታ መቄዶንን በአባታቸው ስም ማዳይ ብሎ ጠራው።

፳፪። ወበ፴ወ፭ቱ ኢዮቤልዩ በሱ

ባዔ ሣልስ በፅዱ ዓመት ነሥአ ሎቱ ራግው ብእሲተ፤

በሠላሳ አምስተኛው ኢዮቤ ልዩ፤ በሦስተኛው ሱባዔ፤ በአ ንደኛው ዓመት ራግው ሚስት አገባ፤

ወስማ ዑራ፤

ስሚም ዑራ ትባላለች፤

ውስተ ዑር ወልደ ኬሴድ፤

ይችውም የኬሴድ ልጅ የዑር ልጅ ናት፤

ወወለደት ሎቱ ወልደ፤

ወንድ ልጅን ወለደችለት፤

ወፀውዐ ስሞ ሴሩግ፤

ስሙንም ሴሩግ፤ አለው ሴሩ ህም ይላል፤ ራግው ሴሩ ህን በሰማንያ ዘመን ወልዶ ታል፤ በሺሕ ስድስት መቶ ሀያ ስምንት ላይ ሰማንያውን ቢያገናኙት ሽሕ ከሰባት መቶ ስምንት ይሆናል፤ ሽሑ ሃያ ኢዮቤልዩ ከሃያ ዘመን ይሆ ናል፤ ሰባቱ መቶ አሥራ አራት ኢዮቤልዩ ከዐሥራ አራት ዘመን ይሆናል፤ ኢዮ ቤልዩን ከኢዮቤልዩ ቢያገና ኙት ዘመኑን ከዘመን ቢገጥ ሙት አርባ ሁለት ይሆናል፤

ይህን በሱባዔ ሲገቡት ስድ ስት ሱባዔ ይሆናል ከተጀ መረ ብሎ እንዲህ አለ ::

ጀቮ፤ ወበሳብዕ ሱባኤሁ ለዝ፤ ኢዮቤልዩ፤

በዚህ ኢዮቤልዩ በሰባተኛው ሱባዔ፤

ወጠኑ ውሉደ ኖኅ ይትቃተሉ፤

የኖኅ ልጆች ሰውን ለመግ ደል፤

ለዔውዎ፤

ለመማረክ፤

ወለቀቲል ፅዱፅዱ እኅዋሁ፤

አንዱም አንዱን ወንድሙን ለመግደል የኖኅ ልጆች ይዋጉ ጀመር፤

ወለክዒወ ደመ ሰብእ ዲበ ምድር፤

የሰውን ደም በምድር ላይ ለማፍሰስ፤

ወለበሊዓ ደም፤

ደምን ለመብላት፤

ወለሐኒፀ አህጉር ፅኑአት፤

የጸኑ አምባዎችን ለመሥ
ራት፤

ጥቅም ወማህፈድ፤

ቅጽሩን ግንቡን ለመሥራት፣

ወለተልዕሎ ብእሲ ላዕለ ሕዝብ፤

አንዱ ወገን በአንዱ ወገን ላይ
በጠላትነት መነሳትን ጀመሩ፤

ወለሠይመ መንግሥት መቅድመ፤

በመንግሥትም ላይ ከአንዱ
አስቀድሞ ለመሾም፤

ወለሐዊረ ፀብእ ሕዝብ ቅድመ
ሕዝብ፤

ሕዝቡ በሕዝብ ፊት ወደሰ
ልፍ ለመሄድ፤

ወአሕዛብ ቅድመ አሕዛብ፤

አሕዛብም በአሕዛብ ፊት ወደ
ሰልፍ ለመሔድ፣

ወሀገር ቅድመ ሀገር ፤

አገርም ከአገር ጋር ለመጣ
ላት፣

ወኵሎ ለአእክዮ ወለአጥርዮ ንዋየ
ሐቅል፤

ሁሉም ክፉ ሥራ ለመሥ
ራት ጋሻ ጦር ለመግዛት፤

ወለምህሮ ውሉዶሙ ፀብአ፣

ልጆቻቸውን ሰልፍ ማስተማር
ጀመሩ፤

ወአኀዙ ይዔውዉ ሀገረ ለሀገር፤

አንዱ አገር አንዱን አገር ይማ
ርክ ጀመር፤

ወለተሣይጦ፣ ለገብርና ወለአመ
ትና፣

ወንዱንም ሴቷንም ባርያ
ይገዙ ጀመር፤

፳፬፤ ወሐነፀ ዑር ወልደ ኬሴድ
ሀገረ ዑራሃ እንተ ከላውዴዎን፤

የኬሴድ ልጅ ዑር በከላውዴ
ዎን ሀገር ያለች ዑራንን ሠራ፤

ወሰመየ ስማ በስመ ዚአሁ ወበ
ስመ አቡሁ፤

ስሟን በሱም በአባቱም ስም
ጠራት፣

ወገብሩ ሎሙ ስብኮዋተ፣

ተመትተው የተሠሩ ጣኦቶ
ችን ሠሩ፤ አንድም ከዋክብተ
ይላል ከዋክብትን አመለኩ፤

ወይሰግዱ ፩ዱ ፩ዱ ለጣዖት ዘገ
ብረ ለርእሱ ስብኮ፤

አንዱም አንዱ ለራሱ መትቶ
ለሠራው ጣኦት፤ ይሰግድ፣
ጀመር፤

ወጠኑ ይግበሩ ግልፎ ወምስለ ወርኩሰ፤

ኃጢአቱን፤ ምስሉን የተቀረጸውን ጣዖት ይሠሩ ጀመረ፤

ወመናፍስት ፀዋጋን ይረድኡ፤

ክፍዎች አጋንንት ይረዷቸው ነበር።

ወያስሕቱ ከመ ይግበሩ አበሳቱ ወርኩሰ ወአበሳ፤

ኀጢአትን በደሉን ይሠሩ ዘንድ ያስታቸው ነበር።

፳፫፤ ወመኰንን መስቴማ ይኄይል ለግብረ ዝንቱ ኵሉ፤

ሁሉን የሚገዛ ዲያብሎስ ይህንን ሁሉ ለመሥራት ይበረታ ነበር ፤አንድም ያኄይል ይላል፤ ጦር ያበረታ ባቸው ነበር።

ወይፈኑ፡ በእደ መናፍስት ለአለ ተውህቡ ታሕተ እዴሁ ለገቢረ ኵሉ ጌጋይ ወኃጢአት፤

ታላላቁን ጥቃቅኑን ኃጢአት ለማሠራት ከሥልጣኑ በታች ላሉ አጋንንት ቃል ይልክ ነበር

ወኵሉ አበሳ ለአማስኖ ወለአኀ ጕሎ ወለክዒወ ደም ዲበ ምድር፤

ኃጢአቱ ሁሉ ሰውን ለማጥፋት በዚህ ዓለም ደም ለማፍሰስ ነው።

፳፬፤ በእንተዝ ተፀውዐ ስሙ ለሴሩህ ሴሩክ፤

ስለዚህ ነገር የሴሩህ ስሙ ሴሩክ ተብሎ ተጠራ፤

እስመ ተመይጠ ኵሉ ለገቢረ ኃጢአት ወጌጋይ፤

ሰው ሁሉ ኀጢአት ለመሥራት ጣዖት ለማምለክ ተመልሶአልና ፤

ወልኀቀ ወኃደረ ውስተ ዑር ዘከላውዴዎን ቅሩበ አበ እመ ብእሲቱ፤

በሚስቱ እናት አባት አጠገብ የከላውዴዎን አውራጃ በምትሆን በዑር አድጎ ኖረ፤

ወኮነ ያመልክ ጣዖተ፤

ጣዖትንም ያመልክ ጀመረ፡

ወነሥአ ሎቱ ሴሩክ ብእሲተ፤

ሴሩክም ሚስትን አመጣ፤

እመ ፴ ወ ፮ ኢዮቤሌዎን በሱ ባዔ ኃምስ በዓመት ቀዳሚሁ ሎቱ፤

በሠላሳ ሰባት ኢዮቤልዩ በአ
ምስተኛው ሱባዔ በመጀመ
ሪያው ዓመት ሚስት አገባ፤

ወስማ ሜልካ ወለተ ካቤር ወለተ
እኅተ አቡሁ፤

የአባቱ የእህት ልጅ የምት
ሆን የካቤር ልጅ ስሟም
ሜልካ ይባላል፤

ወወለደት ሎቱ ናኮርሃ በዓመት
ቀደሚሁ ለገዘ ሱባዔ፤

በዚህ ሱባዔ በመጀመሪያው
ዓመት ናኮርን ወለደችለት፤

ሴሩህ ናኮርን በሠላሳ ሰባት
ዘመን ወልዶታል፤

ሠላሳ ሰባትን ከሺህ ሰባት
መቶ ስምንት ቢያገናኙት
ሺህ ከሰባት መቶ አርባ
አራት ይሆናል፤

ሽሁ ዘመን ሃያ ኢዮቤልዩ
ከኽያ ዘመን ይሆናል፤

ሰባት መቶ ዐስራ አራት
ኢዮቤልዩ ከአሥራ አራት
ዘመን ይሆናል፤

ኢዮቤልዩን ከኢዮቤልዩ ቢያገ
ኛኙት ሠላሳ አራት ይሆናል፤

ዘመኑን ከዘመን ቢያገናኙት
ሠላሳ አራት ይሆናል፤
ሠላሳ አራትና አርባ አራትን
ቢያገናኙት ሰባ ስምንት
ይሆናል፤

አርባ ዘጠኝ ሲነሱለት ሃያ
ዘጠኝ ይቀራል፤ ይኽን በሱ
ባዔ ሲገቡት አራት ሱባዔ
ሆኖ አንድ ዓመት ይተር
ፋል፤ስለ ተጀመረ እንዲህ
አለ።

፳፯፤ ወልህቀ ወንደረ ውስተ ዑር
ዘከላውዴዎን፤

አድጎ በጉልምስናው ጊዜ በከ
ላውዴዎን አውራጃ በዑር
ኖረ፤

ወመሀሮ አቡሁ ጉሣሄሙ
ለከዋክብት፤

አባቱ ከዋክብትን መቁጠር
አስተማረው፤

ለተማርዮ ወለተሰግሎ፤

ሚርትን ጥንቆላን አስተማ
ረው፤

በተአምረ ሰማይ፤

በወሐይ በጨረቃ ምልክት
አስተማረው።

፳፰፤ ወበ፴ ወ ፯ ኢዮቤልዩ በሱ
ባዔ ሳድስ በ፩ ዓመት ነሥአ
ሎቱ ብእሲተ፤

በሠላሳ ሰባተኛው ኢዮቤልዩ
በስድስተኛው ሱባዔ በመጀመ
ሪያው ዓመት ሚስት አገባ፤

ወስማ ኢዮስካ
ስሟም ኢዮስካ ይባላል፤

ወለተ ኒስቴግ ዘከለዳውያን፤

ይቺውም ከከለዳውያን ወገን
የሚሆን የኒስቴግ ልጅ ናት፤

ወለደት ሎቱ ወልደ ታራሃ
በዓመት ሳብዕ ዘዝ ሱባዔ፤

በዚህ ሱባዔ በሰባተኛው
ዓመት ታራ የሚባል ወንድ
ልጅ ወለደችለት፣

ናኮር ታራን በስልሳ ሁለት
ዘመን ወልዶታል፣

ስልሣ ሁለትን ከሺህ ሰባት
መቶ አርባ አራት ቢያገና
ኙት ሺሕ ከስምንት መቶ
ስድስት ዘመን ይሆናል፣

ይህን በኢዮቤልዩ ቢገቡት
ሰላሳ ሰባት ኢዮቤልዩ ሆኖ
አርባ ዘጠኝ ዘመን ይተር
ፋል፣ በሱባዔ ሲገቡት ሰባት
ሱባዔ ይሆናል፡፡

፳፱፤ ወፈነወ መኰንን መስቴማ
ቋዓተ ወአዕዋፈ፣

ሰይጣን ቁራዎችን፣ ዎፎችን
ሰደደ፣

ከመ ይብልዑ ዘርአ ዘይዘራዕ
ውስተ ምድር ለአማሰኖ ምድር፤

ምድርን ለማጥፋት በምድር
ላይ የሚዘራውን ዘር ይበሉ
ዘንድ ሰደደ፤

ከመ ይኂድዎሙ ለዕጉለ ሰብእ
ትግብርቶሙ፤

የሰዎች ልጆች የደከሙበትን
ይቀሟቸው ዘንድ፣

ዘእንበለ ይሕርሱ ወይዝርኡ ዘርዐ
የአርሩ ቋአት ወአዕዋፍ እምገጸ
ምድር፣

ቁራዎች ዎፎች ሳያርሱ ዘሩን
ከምድር ይለቅሙ ጀመር፡፡

በእንተዝ ጸውዐ ስሞ ታራ፤

ስለዚህ ነገር ናኮር ስሙን
ታራ አለው፤

ዖፍ ጽኑ ማለት ነው፤

እስመ ያስተዔንስዎሙ ለሰብእ
ቋአት ወአእዋፍ፤

ዎፎች ቁራዎች ዘሩን

እየለቀሙ ሰምችን ያስቸግ ሯቸው ነበርና፤

ወይበልዑ ቦሙ ዘርዖሙ ፤

ዘራቸውን ይበሉባቸው ነበ ርና።

፴፤ወአነዙ ዓመታት ይዕበሩ እምቅድመ ገጸሙ ለአዕዋፍ፤

ከምፎች ፊት የተነሣ ዘመኖች ቀጠና (ድርቅ) ይሆኑ ጀመር።

ወኵሉ ፍሬ ዕዕ ይበልዑ እምአ ዕዋም በኃይል ዓቢይ፤

በኃይላቸው ዛፉን እየጣሉ የዕንጨቱን ፍሬ ሁሉ ይበሉ ነበር ፤

ወእመ ክህሉ አድኅኖ ኅዳጠ እም ኵሉ ፍሬ ምድር በመዋዕሊሆሙ፤

በዘመናቸው ከእንጨት ፍሬ ሁሉ ጥቂት ማዳን ቢችሉ በጽኑ ኃይል ነበር፤

ወበ ፴ ወ ፱ ኢዮቤልዩ በሱባዔ ካልዕ በቀዳሚት ዓመት ነሥአ ሎቱ ታራ ብእሲተ፤

በሠላሳ ዘጠነኛው ኢዮቤልዩ በሁለተኛው ሱባዔ በመጀመ ራይቱ ዓመት ታራ ሚስት አገባ፤

ወስማ ኤድና፣

ስሟ ኤድና ትባላለች፤

ወለተ አብራም ወለተ እኅተ አቡሁ፤

ይህችውም የአባቱ የእኅት ልጅ የምትሆን የአብራም ልጅ ናት፤

ወበዓመት ሳብዕ ዘዝ ሱባዔ ፤

በዚህ ሱባዔ በሰባተኛው ዓመት፤

ወለደት ሎቱ ወልደ፤

ወንድ ልጅ ወለደችለት፤

ወፀውዐ ስሞ አብራም በስሙ አቡሃ ለአሙ፤

በናቱ አባት ስም ስሙን አብራም አለው፤

ታራ አብራምን በ፳ ዘመን ወልዶታል፤

ሺህ ስምንት መቶ ስድስት ከሰባው ዘመን ጋር በተገናኘ ጊዜ ሺህ ስምንት መቶ ሰባ ስድስት ዘመን ይሆናል፤ ይህ ሠላሳ ስምንት ኢዮቤ ልዩ ይሆናል፤ ወደኋላ የቀረ የታራን ዘመን ጨምሮ ቢቆ ጥሩ የሙሴ ልደት ይገኛል፤

አሪት በመቶ ዘመን ወለደው ይላል፤ ከዚህ በፊ ዘመን ወለደው ይላል፤የቀረው ሠላሳው ዘመን ነው፤ ሠላሳው ሲጨመር ሺሕ ከዘጠኝ መቶ ከስድስት ዘመን ይሆናል፤ ዓለም በተፈጠረ በሺሕ ከዘጠኝ መቶ ከስድስት ዘመን ታራ አብር ሃምን ወለደው፤ አብርሃም ይስሐቅን በመቶ ዘመን ወለደው፤ ይስሐቅ ያዕቆብን በስልሳ ዘመን ወለደው፤ ያዕቆብም ሌዊን በሰማንያ አምስት ዘመን ወለደው፤ ሌዊ ቀዓትን በዐርባ አራት ዘመን ወለደው፤ ቀዓት እንበረምን በስሳ፤ አምስት ዘመን ወለደው፤ እንበረምም ሙሴን በሰባ ዘመን ወለደው። ይህ ሁለት ሺሕ ከሦስት መቶ ሠላሳ ዘመን ይሆናል፤ ይህን በኢዮቤልዩ ቢቆጥሩት ዐርባ ስድስት ኢዮቤልዩ ሆኖ ሃያ ሰባት ዘመን ይተርፋል፤ ዘመነ አበው ሶስት ሽሕ ከስምንት መቶ ኃምሳ ዘመን ነው፤ዘመነ ሙሴ መቶ ሃያ፤ ዘመነ መሳፍንት አራት መቶ ሀምሳ፤ ዘመነ ነገሥት አምስት መቶ ዐስራ ሦስት፤ ዘመነ ካህናት ዐራት መቶ ዘጠና፤ ዘመነ ቄዋዊ ሰባ ሰባት፤ ይህ አምስት ሺሕ ከአምስት መቶ ዘመን ይሆናል።

እስመ ሞተ ዘእንበለ ይፀነስ ወልደ ወሰቱ፤

የልጅ ልጁ ሳይፀነስ ሙቷ ልና ስሙን በእናቱ አባት ስም አብራም አለው።

፴፩፤ ወእንዘ ገንቱ ሕፃን ያእምር ስሕተተ ምድር፤

ያም ልጅ አብራም ፤የምድርን ስሕተት ያውቅ ጀመር፤ አንድም ስሕተት እንደሆነ አወቀ፤

ከመ ኵሉ ይስሕት በድኅሬሆሙ ለግልፎ ወድኅረ ርኵስ ፥

ኀጢአትን ጣዖትን በመከተል ሰው ሁሉ እንዲስት አወቀ።

፴፪፤ ወመሐሮ አቡሁ መጽሐፈ፤

ምንም መምለኬ ጣዖት ቢሆን መጽሐፈ አበው በእጁ ነበረና አባቱ መጽሐፍ አስተማረው፤

ወወልደ ፪ቱ ሱባዔ ዓመት ውእቱ፤

የሁለት ሱባዔ ዘመን ልጅ ነበር፤

ወተፈልጠ እምድኅረ አቡሁ ከመ ኢይስግድ ምስሌሁ፣

ከሱ ጋራ ለጣዖት እንዳይሰ ግድ አባቱን ከመከተል ተለየ ፤ አንድም እምድረ አቡሁ ከአ ባቱ አገር ተለየ።

፴፫፣ ወአኀዘ ይጸሊ አብራም ኀበ ፈጣሬ ኵሉ ከመ ያድኅኖ እምስሕተተ ውሉደ ሰብእ፤

የሰዎች ልጆች ሁሉ ከሚበ ድሉት በደል ያድነው ዘንድ አብራም ወደፈጣሪው ይጸ ልይ ጀመር ፤

ወከመ ኢይረድ መክፈልቱ ውስተ ስሒት ድኅረ ርኵስ ወምናኬ፣

ርኩስ ምኑን የሚሆን ጣዖ ትን በመከተል ዕጣው ወደስ ሕተት እንዳይሆን ሁሉን ወደ ፈጠረ ወደ እግዚአ ብሔር ይጸልይ ጀመር፤

፴፬፣ወበጽሐ ጊዜ ዘርእ ለዘሪዕ ውስተ ምድር፣

በምድር ዘርን ለመዝራት የሚዘሩበት ጊዜ ደረሰ፤

ወወጽኡ ኵሎሙ ኀቡረ ከመ ይዕቀቡ ዘርዖሙ እምገጸ ቋዓት፤

ዘራቸውን ካሞሮች ፊት ይጠብቁ ዘንድ ሁሉም አንድ ሁነው ወጡ።

፴፭፣ወወጽአ አብራም ምስለ እለ ወጽኡ ሕፃናት፤

አብራምም ከወጡት ልጆች ጋራ ወጣ፣

ወዝንቱ ሕፃን ወልደ ፲ወ፬ ዓመት፤

አብራምም የዐሰራ አራት ዓመት ልጅ ነበር፤

ወደመና ቋዓት መጽኡ ከመ ይብ ልዑ ዘርአ፤

ብዙ ቁራዎች ዘሩን ሊለ ቅሙ መጡ፣

ደመናን ብዙ ሲል ነው ፤

ወአብራም ይረውጽ በአንፃሪሆሙ ዘእንበለ ይንበሩ ውስተ ምድር፤

ከምድር ሳያርፉ አብራም በፊታቸው ይሮጥ ነበር፤

ወይኬልሕ ላዕሌሆሙ ዘእንበለ ይንበሩ ዲበ ምድር ለበሊዓ ዘርዕ፣

ዘሩን ለመልቀም በምድር ላይ ሳያርፉ አብራም በነዚያ ላይ ይጮህ ነበር፤

ወይብል ኢትረዱ ግብኡ ውስተ

መካን ጎበ መጻእክሙ፤

ወደመጣችሁበት ቦታ ተመ
ለሱ እንጅ ወደ ምድር አት
ውረዱ ይላቸው ነበር፤

ወተመይጡ፤

እነሱም ተመለሱ።

፴፮፤ወገብሩ በይእቲ ዕለት በደመና
ቋዓት ሰብአ፤

በዚህች ቀን ብዙ ቁራዎችን
ለመከልከል ሰውን አስቀ
መጡ፤

ወኢነበረ እምኵሉ ቋዓት ውስተ
ኵሉ ገራውህ ጎበ ሀሎ አብራም
ወኢአሐዱ፤

ከቁራዎች ሁሉ አብራም ከአ
ለበት እርሻ አንድ ቁራ
አላረፈም።

፴፯፤ወይሬእይም ኵሎሙ ሰብአ
አለ ነበሩ ምስሌሁ ውስተ ኵሉ
ገራውህ አንዘ ይኬልህ፤

አብራምን ከርሱ ጋራ ያሉት
ሁሉ በርሻው ሁሉ ሲጮህ
ያዩት ነበር ፤

ወይቤሎሙ አብራም ለኵሉ
ቋዓት ተመየጡ፤

አብራምም አሞሮችን ሁሉ
ተመለሱ ይላቸው ነበር፤

ወዓብየ ስሙ ለአብራም በኵሉ
ምድረ ከላውዴዎን፤

በከላውዴዎን አውራጃ ሁሉ
የአብራም ስሙ ከበረ ገነነ።

፴፰፤ወመጽኡ ጎቤሁ በዓመት
ዝንቱ ኵሎሙ አለ ይዘርኡ፤

የሚዘሩት ሰዎች ሁሉ በዚህ
ወራት ወደሱ ይመጡ ነበር፤

ወሀሎ አብራም የሐውር ምስሌ
ሆሙ እስከ አመ የኃልቅ ጊዜ
ዘርእ፤

የዘሩ ጊዜ እስኪፈጸም ድረስ
ከነዚያ ጋራ ይሔድ ነበር፤

ወዘርዐ ምድሮሙ ፤

ምድራቸውን ዘሩ ፤

ወአብኡ በውእቱ ዓመት እክለ
እኩለ፤

በዚህ ዘመን የሚበቃ እህል
አገኙ አገቡ፤

ወበልዑ ወጸግቡ፤

ይህን በልተው ጠገቡ።

፵፱፤ወበ፩ ዓመት ዘሱባዔ ሐምስ
መሀረ አብራም ለለይገብሩ ንዋየ

አልህምት በኪነተ ዕዕ፤

በአምስተኛው ሱባዔ ባንዱ ዓመት አብራም ሰደቃ ገበታና የበሬ ዕቃ ለሚሰሩ ሰዎች ሞፈር ቀምበር መብሳት እርፍ ማቅናት ድግር መጥረብ መብሳት የእንጨት ሥራ አስተማራቸው።

፭፤ወገብሩ ንዋየ በመልዕልተ ምድር፤

በምድር ላይ የሚያገለግሉትን ዕቃ፤

በአንጻረ ድጉር እርፈ፤

በድግሩ አንጻር እርፉን ሠሩ፤ አንድም በአንጻረ እርፍ ድጉረ ይላል፤ በእርፉ አንጻር ድግሩን ያኖሩ ዘንድ አስተማረ፤

ከመ ያንብር ላዕሌሁ ዘርዐ፤

ዘሩን በላዩ ላይ ያኖር ዘንድ፤

ወያውርድ እምውስቴቱ ዘርዐ ውስተ ከተማ እርፍ፤

ማረሻውን ፈንቅሎ በሚገባበት በእርፉ ጫፍ ዘሩን ያወርድ ነበር፤

ወይትኃባዕ ውስተ ምድር፤

በምድር ውስጥ ዘሩ ከአዕዋፍ ይሠወር ነበር።

ወኢፈርኑ እንከ ሰብእ እምገጸ ቋዓት፤

ከዚያ በኋላ ሰዎች ከቁራ ወፎች ፊት የተነሣ አልፈሩም፤

ወገብሩ ሰብእ ከመገዘ ላዕለ ኵሉ ድጉረ እርፍ፤

በእርፍ ባለ በድግሩ ላይ እንዲህ አደረጉ፤

ወድጉረ እርፍ አንበሩ መልዕልተ ምድር፤

በእርፍ ላይ ያለ ድግሩን ከምድር ላይ አደረጉ።

፯፩፤ወዘርዐ ዘርዐ ወገብሩ ኵሉ ምድር ኵሎ ዘከመ አዘዘሙ አብራም፤

አብራም እንዳዘዛቸው የሥራውን ዕቃ ሁሉ ሠሩ፤

ወኢፈርኑ እንከ እምቋዐት፤ ከዚያ በኋላ ከቁራዎች የተነሣ አልፈሩም።

፯፪፤ወኮነ በሱባዔ ሳድስ በሳብዕ ዓመቱ ሎቱ ይቤሎ አብራም ለታራ አቡሁ፤

በስድስተኛው ሱባዔ በሰባተ

ኛው ዓመት አብራም አባቱ ታራን እንዲህ አለው፤

እንዘ ይብል አባ ወአቡየ፤

አባቴ ሆይ አለው፤

ወይቤ ነየ አነ ወልድየ፤

ልጄ!እነሆ እኔ አለሁ አለው፣

ወይቤ ምንት ረድኤት ወተድላ ለነ እምእሉ ጣዖታት ዘአንተ ታመልክ ወትሰግድ ቅድሜሆሙ፣

አንተ ከፊታቸው ከምትሰ ግድላቸው ከምታመልካቸው ጣዖታት ተድላ ደስታ ረድ ኤት የምናገኘው ምንድነዉ አለው፤

እስመ አልቦ ላዕሌሆሙ ምንትኒ መንፈስ፤

በነዚያ ላይ ምንም ምን ቃል እስትንፋስ የለምና፤

እስመ ስግመት እሙንቱ፣

እነሱ ዲዳዎች ደንቆሮዎች ናቸውና፤

ወስሕተተ ልብ እሙንቱ፤

ልቡናን የሚያስቱ ናቸው፤

ኢታምልክዎሙ፣

አታምልኳቸው፡፡

፵፫፤ አምልኩ እምላከ ሰማይ ዘያወርድ ዝናመ ወጠለ ዲበ ምድር፤

ዝናም ለዘርዕ ጠል ለመኸር የሚሰጥ ሰማይን የፈጠረ አምላክን አምልኩ እንጂ፣

ወይገብር ኵሎ ላዕለ ምድር፣

በምድር ላይ ሁሉን ያደር ጋል፤

ወኵሎ ፈጠረ በቃሉ፤

ሁሉን በቃሉ የፈጠረ፤

ወኵሉ ሕይወት እምቅድመ ገጹ፣

ከገጸ ረድኤቱ የተነሣ ሕይ ወት ሁሉ ከሱ ይገኛል፡፡

፵፬፤ ለምንት አንትሙ ታመልኩ እለ አልቦሙ መንፈስ ላዕሌሆሙ፤

በላያቸው ላይ ቃል እስትን ፋስ የሌለባቸው ጣዖታትን ለምን ታመልካላችሁ?

እስመ ግብረ እደ ሰብእ እሙንቱ፤

እነሱ የሰው እጅ ሥራ ናቸ ውና፤

ወዲበ መታክፍቲክሙ አንትሙ ትፀውርዎሙ ፤

እናንተ በትከሻችሁ ላይ ትሸ ከሟቸዋላችሁ፤

ወአልቦ እምኔሆሙ ለክሙ ረድኤት፤

ለእናንተ የሚሆን ረድኤት ከነሱ አይገኝም፤

ዘእንበለ ኃጣር ዓቢይ ለአለ ይገብርዎሙ፤

ለሚሰሯቸው ሰዎች ፅኑዕ ተዋርዶ ናቸው እንጅ ፤ ወስሕተተ ልብ ለአለ ያመልክ ዎሙ፤

ለሚያመልኩባቸውም ሰዎች የልቡና ስህተት ናቸው፤ ኢታምልክዎሙ፤

እንዲህ እንዲህ ከሆኑ እን ዲህ እንዲህ ናቸውና አታም ልኪቸው አለ።

፵፩፤ ወይቤሎ አቡሁ ፤

አባቱ እንዲህ አለው፤

ወአነሂ አአምር ወልድየ፤

ልጄ ! ከጣዖቱ የምናገኘው ተድላ ደስታ እንደሌለ እኔም አውቃለሁ፤

ምንተ እሬሲ ለሕዝብ እለ ረሰዩኒ አትለአክ ቅድሜሆሙ፤

ነገር ግን በፊታቸው አገ ልግል ዘንድ ካህነ ጣዖት አድርገው ለሾሙኝ ሕዝብ ምን ላድርግ፤

ወእመ ነገርክዎሙ ጽድቀ ይቀት ሉኒ፤

እውነት ነገርንም ከነገርኪቸው ይገድሉኛል፤

እስመ ተለወት ነፍሶሙ ኀቤ ሆሙ ከመ ያምልክዎሙ ወይሰብ ሕዎሙ፤

ያመሰግኗቸው ያመልኩአቸው ዘንድ ልቡናቸው እነዚያን ተከትሏልና፤

አርምም ወልድየ ከመ ኢይቅት ሉከ፤

ልጄ እንዳይገድሉህ ዝም !

በል ::

፵፪፤ ወነገረ ዘንተ ነገረ ለፀቱ አኃዊሁ፤

ይህን ነገር ለሁለቱ ወንድ ሞቹ ነገራቸው፤

ተምዑ ላዕሌሁ፤

በሱ ላይ ተቆጡ፤

ወአርመመ፤

ዝም አለ።

፵፫፤ ወበአርብዐ ኢዮቤልዩ በሱባዔ ካልእ በሳብእ ዓመቱ ሎቱ ነሥአ

አብራም ብእሲተ፤

በአርባ ኢዮቤልዩ በሁለት ሱባዔ በሰባተኛው ዓመት አብራም ሚስት አገባ፤

ወስማ ሶራይ፤

ስሚ ሶራ ይባላል፡፤

ወለተ አቡሁ፤

ያባቱ ልጅ ናት፤

ወኮነቶ ሎቱ ብእሲተ፤

ለእሱ ሚስት ሆነችው።

፱፤ወአራን እትሁ ነሥአ ሎቱ ብእሲተ በዓመት ሠላስ ዘሱባዔ ሣልስ፤

በሶስተኛው ሱባዔ በሦስተኛው ዓመት ወንድሙ አራን ሚስት አገባ፤

ወበሱባዔ ሣልስ ወለደት ሎቱ ወልደ በዓመት ሳብዕ ዘሱባዔ ዝንቱ፤

በዚህ ሱባዔ በሰባተኛው ዓመት በሦስተኛው ሱባዔ ወንድ ልጅ ወለደችለት፤

ወጸውዐ ስሞ ሎጥ፤

ስሙን ሎጥ አለው፤

ወናኮር እትሁ ነሥአ ሎቱ ብእሲተ፤

ናኮር ወንድሙ ሚስት አገባ።

ምዕራፍ ፲፭

፩፤ወበዓመት ዘኀ ዘሕይወተ አብራም፤

አብራም በሕይወት በኖረበት በስሳ ዘመን፤

ውእቱ ሱባዔ ራብዕ፤

ይኸውም አራተኛ ሱባዔ ነው፤

በዓመት ራብዕ ሎቱ ተንሥአ አብራም በሌሊት፤

ባራተኛው ዓመት አብራም በሌሊት ተነሥቶ፤

ወአውዐየ ቤተ ጣዖታት፤

የጣዖታቱን ቤት አቃጠለው፤

ወአውዐየ ኵሉ ዘውስተ ቤት፤

በቤት ውስጥ ያለውን ዕቃ ሁሉ አቃጠለ፤

ወሰብአሰ አልቦ ዘአእመረ ፤ ያወቀ ሰው ግን የለም።

፪፤ወተንሥኡ ሌሊተ፤

ሌሊት ተነሡ፤

ወፈቀዱ ከመ ያድኅኑ አማልክ ቲሆሙ እማእከለ እሳት፤

ጣዖታቲን ከእሳቱ መካከል ያድኑ ዘንድ ወደዱ።

፫፤ወሠረረ አራን ከመ ያድኅኖሙ፤

አራን ያድናቸው ዘንድ ፈጥኖ ሄደ ተወረወረ፤

ወነደ እሳት ላዕሌሁ፤

እሳቱ በሱ ላይ ነደደ፤

ወውዕየ በእሳት፤

በእሳት ተቃጠለ፤

ወሞተ በኢኑር ዘከላውዴዎን፤

በከላውዴዎን ውስጥ ባለች ኢኑር ሞተ፤

በቅድመ አቡሁ ታራ፤

ባባቱ ታራ ፊት፤

ወቀበርዎ በኢኑር ዘከላዴዎን፤

በከላውዴዎን ውስጥ ባለች ኢኑር ቀበሩት።

፬፤ወወጽአ ታራ እምነ ዑር ዘከላውዴዎን፤

ታራ በከላውዴዎን ውስጥ ከአለች ዑር ወጣ፤

ውእቱ ወውሉዱ ከመ ይምጽኡ ውስተ ምድረ ሊባኖስ፤

እሱ ልጆቹ ወደምድረ ሊባኖስ ወጡ፤

ወውስተ ምድረ ከነአን፤

ወደከነአንም አውራጃ፤

ወውስተ ምድረ ካራን፤

ወደካራን ይመጡ ዘንድ።

፭፤ወነደረ አብራም ምስለ ታራ አቡሁ ውስተ ካራን ፸ተ ሱባዔ ዓመታት፤

አብራም ከአባቱ ታራ ጋር ሁለት የዘመን ሱባዔ አሥራ አራት ዓመት በካራን ተቀመጠ።

፮፤ወበሳድስ ሱባዔ በዓመት ሐምሳ ተንሥአ አብራም፤

በስድስተኛው ሱባዔ ባምስተኛው ዓመት አብራም ተነሣ ፤

ወነበረ በሌሊት በሠርቀ ወርኅ ላብዕ ከመ ያበይን ከዋክብተ እምነግህ እስከ ሠርክ፤

ከዋክብትን ከሠርክ እስከ ነግህ ድረስ ይቆጥር ዘንድ በሰባተኛው ወር በጥቅምት በሌሊት ተቀመጠ፤

ከመ ይርአይ ምንት ይከውን ግብረ ዓመት በዝናማት፤

የዘመኑን ሥራ ምን እንደሆነ ያይ ዘንድ ማለት ዝናም ይዘንብም፤ አያዘንብም እንደሆነ፡

፮፤ ወሀሎ ውእቱ ባሕቲቱ ይነብር ወያበይን፤

ብቻውን ተቀምጦ ይቆጥር ነበር፤

ወመጽአ ውስተ ልቡ ቃል፤

በልቡ ቃል ታሰበው፤

ወይቤ ኵሉ ተአምረ ከዋክብት ወተአምሪሃ ለወርኀ ወለፀሐይ ኵሉ በእደ እግዚአብሔር፤

የከዋክብት የፀሐይ የጨረቃ ምልክት በሱ በእግዚአብሔር ሥልጣን ተይዞአል፤

ለምንት አነ እትነሠሥ ለእመ ፈቀደ ያዝንም ነግሀ ወሠርክ፤

እኔ ለምን እመራመራለሁ፤

በሠርክ በነግህ ሊያወርድ ቢወድ ያዝንም፤ አንድም የግንቦት የሰኔ የጥቅምት የኅዳር ዝናም ሊያዘንም ቢወድ ያዝንም፤

ወእመ ፈቀደ አያውርድ፤

እንዳያዘንምም ቢወድ አያዝንም፤

ኵሉ ውስተ እዴሁ፤

ሁሉ በሱ እጅ ነው።

፯፤ ወጸለየ በዛቲ ሌሊት ፤

በዚህችም ሌሊት ለመነ፤

ወይቤ አምላኪየ አምላኪየ አምላክ ልዑል፤

ልዑል ገናና የምትኾን ፈጣሪዬ ፈጣሪዬ፤

አንተ ባሕቲትከ ሊተ አምላክ፤

የኔ ፈጣሪ አንተ ብቻ ነህ፤

ወአንተ ኵሉ ፈጠርከ፤

ሁሉን አንተ ፈጠርህ፤

ወግብረ እደዊከ ኵሉ ኮነ፤

የእጅህ ሥራ ሁሉ ጸንቶ ኖረ፤

ኪያከ ወመለኮተከ ኃረይኩ አነ፤

እኔ አንተን ጌትነትህን ማም ለክ ወደድኩ፤

አድኅነኒ እምእደ መናፍስት እኩያን እለ ይሜለሑ፤

ውስተ ሕሊና ልበ ሰብእ፤

በሰው ልቡና ከሚሠለጥኑ

ክፎዎች አጋንንት አንተ አድ
ነኝ፤

ወኢያስሕቱኒ እምድኅሬክ አምላ
ኪየ፤

ፈጣሪዬ አንተን በሕግ
በአምልኮት ከመከተል እንዳ
ያስቱኝ አድነኝ፤

ወረስየኒ ኪያየ ወዘርዕየ አንተ
ለዓለም ኢንስሐት እምይእዜ ወእ
ስከ ለዓለም፤

እኔንም ልጆቼንም አንተ ከዛሬ
ጀምሮ ለዘለዓለም እንዳን
ስት እንዳንበድል አድርገን
አለ።

፱፤ወይቤ እመ እገብዕሁ ውስተ
ዑር ዘከላውዴዎን፤

በከላውዴዎን ውስጥ ወደአ
ለች፤ ዑር ብመለስ፤

እሙንቱ የሐሥሡ ገጽየ ከመ
እግባዕ ኀቤሆሙ፤

በርሳቸው አድር ዘንድ ሰው
ነቴን ይፈልጋሉ ይሻሉ፤
ወሚመ እንበር ዝየ በዝ መካን
ፍኖተ ርቱዐ በቅድሜክ ኪያሃ
ሠርጎ፤

ወይም እኔ በዚህ ቦታ እቀ
መጥ ዘንድ በፊትህ ጐዳናየን
አቅናልኝ፤

በእደ ገብርክ ግበር፤

በኔ ቃል ይህንን አድርግ፤

ወኢይሑር በስሐተተ ልብየ አምላ
ኪየ፤

ፈጣሪየ፣ በልቡናየ ስሕተት
ጸንቼ እንዳልኖር አለ።

፲፤ወውእቱ ሶበ ፈጸመ ተናግሮ
ወጸልዮ፤

እሱም ይሽንን ተናግሮ ጸልዮ
ከፈጸመ በኋላ ፤

ወናሁ ቃለ እግዚአብሔር ተፈነወ
ኀቤሁ በእዴየ፤

እነሆ የእግዚአብሔር ቃል
ወደሱ በኔ ቃል መጣ፤

እንዘ ይብል ፃዕ እምድርክ፤

ከሀገርሁ ና ውጣ ብሎ፤

ወእምኀ ትዝምድክ ወእምኀ ቤተ
አቡክ፤

ከአባትህ ቤት ከወገንህ ከሀገ
ርህ ተለይተህ ና፤

ውስተ ምድር እንተ አርእየክ፤
እኔ ወደማሳይህ ሀገር ና፤

ወእሬስየክ ሕገበ ዓቢየ ወብዙኃ፤
ብዙ ደግ ወገን አደርግሀለሁ፤

ወእባርክክ፤

አክብርሃለሁ፤

ወአዐቢ ስመክ፤

ስምህን አከብረዋለሁ ከፍ ከፍ አደርገዋለሁ አገነዋለሁ፤

ወትከውን ቡሩክ ውስተ ኵሉ ምድር፤

በሀገሩ ሁሉ የክበርህ ትሆና ለህ።

፲፩፤ወይትባረኩ ብክ ኵሎሙ አሕዛበ ምድር፤

በዚህ ዓለም የሚኖሩ አሕዛብ ሁሉ ባንተ ይክብራሉ ይመራረቃሉ፤

ለእለ ይባርኩክ እባርኮሙ፤

አንተን የሚመርቁህን እመር ቃቸዋለሁ አከብራቸዋለሁ፤

ወለእለ ይረግሙክ እረግሞሙ፤

አንተን የሚረግሙህን እረግ ማቸዋለሁ አጠፋቸዋለሁ፤

ወእከውነከ ለክ አምላክ ወለውሉ ድክ ወለውሉደ ውሉድክ፤

ላንተም ለልጆችህም ለልጅ ልጆችህም ፈጣሪህ እኔ ነኝ፤

ወለኵሉ ዘርዕክ፤

ላንተ ለወገኖችህም ሁሉ፤

እምድኅሬክኒ አነ አምላክ ፤

ከአንተ በኋላም ለሚነሱ ፈጣሪ እኔ ነኝ፤

ኢትፍራህ እምይእዜ ወእስክ ኵሉ ትዝምደ ምድር ፤

ከዛሬ ጀምሮ እስከ ልጅ ልጅ ዘመን ድረስ አት ፍራ ፤

አነ አምላክክ፤

ፈጣሪህ እኔ ነኝ።

፲፪፤ወይቤለኒ እግዚአብሔር አም ላክ ፍታህ አፋሁ፤

ሁሉን የፈጠረ እግዚአብሔር ምሥጢር ግለጥለት አለኝ።

ወእዘኒሁ ይስማዕ፤

ዕዝነ ልቡናውን እንዲሰማ አድርገው፤

ወይንብብ በልሳኑ በልሳን እንተ ታስተርኢ፤

በተረዳች ቋንቋ ባንደበቱ ይና ገር ዘንድ ግለጥለት አለኝ።

እስመ አዕረፈ እምአፈ ኵሉ ውሉደ ሰብእ ዘእምዕለተ ድቀት፤

ጥቅመ ሰናያርን ፤ ነፋስ ገልብጦ ከጣለው ጀምሮ

የሰው ልጅ ሁሉ ከሚናገ
ርበት ቋንቋ ተለይቷልና።

፲፫ ፤ወፈታሕኩ አፋሁ ወእዘኢሁ
ወከናፍሪሁ ፤

አፉን ጆሮውን አንደበቱን
ገለጽኩለት ማለት ምስጢር
ገለጽሁለት ፤ሲል ነው ፤

ወአኃገዝኩ እትናገር ምስሌሁ
አብራይስጠ በልሳነ ፍጥረቱ ፤
በተፈጠረበት በዕብራይስጥ
ቋንቋ ከእሱ ጋራ እናገር
ጀመርኽ ፤

እንተ ታስተርኢ ፤

ቀድሞ በሰው ሁሉ አንደበት
የምትነገር ፤ ዛሬም በመላእ
ክት አንደበት የምትነገር ፤

እስመ አዕረፈ እምአፈ ኩሉ ፤
ተፀርዓ ፤ ተንጕሰ ሲል ነው ፤
ከማየ አይኅ ከጥቅመ ሰናያር
ጀምሮ የዕብራይስይጥ ቋንቋ
ከሰው ሁሉ አንደበት ጠፍቶ
ነበርና ፤

ወነሥአ መጻሕፍተ አበዊሁ
ወጽሑፋት አማንቱ አብራይስጠ ፤
ያባቶቹን መጽሐፎች ወሰደ ፤
እነዚህም የዕብራይስጥ ቋንቋ
የተጻፈባቸው ናቸው ፤

ወደገሞን ወአንዘ ይተመሀርን
እምአሜሃ ፤

አንበቦን ሲል ነው ፤ ከዝያች
ቀን ጀምሮ ዳግመኛ ያነባ
ቸው ይማራቸው ጀመር ፤

ወእነ አየድኦ ኩሉ ዘይሰአና ፤

የፀነነውን እኔ እነግረዋለሁ ፤

ወተመሀሮን ፮ተ አውራኃ ዝናም ፤

ዝናም በሚዘንምባቸው በስድ
ስቱ ወራት ተማራቸው ።

፲፬ ፤ወኮነ በዓመት ሳብዕ ዘሱባዔ
ሳድስ ፤

በሰባተኛው ዓመት በስድስተ
ኛው ሱባዔ እንዲህ ሆነ ፤
ወተናገረ ምስለ አቡሁ ፤

ከነዚያ ያለውን ተናገረ ብሎ
አመጣው ፤

ወአይድኦ ለአቡሁ ከመ የሐውር
ውእቱ እምካራን ለሐዊረ ምድረ
ከነአን ፤

ከካራን ወደከነአን ለመሄድ
እንደተነሣ ነገረው ፤

ይርአይ ወይግባዕ ኀቤሁ ፤

አይቶ ወደሱ ይመለስ
ዘንድ ።

፲፫፤ወይቤሎ አቡሁ ታራ ሑር በሰላም አምላከ ሰላም ያርትዕ ፍናዊከ፤

አባቱ ታራ በፍቅር በደስታ ሂድ ጎዳናህን ፈጣሪ ያቅና ልህ አለው፤

ወእግዚአብሔር የሃሉ ምስሌከ፤

እግዚአብሔር በረድኤት ካንተ ጋር ይኑር፤

ወይትመሐፀንከ እምኵሉ እኩይ፤

ከክፉው መከራ ሁሉ እንደ አደራ ይጠብቅህ፤

ወየሀብከ ሳዕሌከ ሣህለ ወምሕረተ ወሞገሰ በቅድመ እለ ይሬእዩከ፤

በሚያውቁህ ሰዎች ፊት ባለሟልነትን ቸርነትን ለአንተ ይስጥህ፤

ወኢይኰንኑከ ኵሉ ውሉደ ሰብእ ለአእከኖ ዲቤከ፤

ባንተ ላይ ክፉ ለማድረግ የሰዎች ልጆች ሁሉ አይሰል ጥኑብህ፤

ሑር በሰላም፤

በፍቅር በደስታ ሂድ።

፲፬፤ወእመ ርሲከ ምድረ አዳመ ለአዕይንቲከ ለኃዲር ውስቴታ፤

በሷ ለመኖር በዓይንህ መልካም ሀገር ብታይ፤

ነዓ ወንሥአኒ ኀቤከ ምስሌከ፤ መጥተህ ወደአንተ ውሰደኝ፤

ወንሥኦ ለሎጥ ምስሌከ ወልደ አራን እኁከ ለከ ወልደ ይኩንከ፤ ለአንተ ልጅ ይሆንህ ዘንድ፤ የወንድምህ የአራንን ልጅ ሎጥንም ካንተ ጋር ውሰደው፤

ወእግዚአብሔር ምስሌከ፤

እግዚአብሔር በረድኤት ካንተ ጋራ ይኑር፤

ወናኮርሃ እኅዋከ ሀድግ ኀቤየ እስከ ትገብእ በሰላም፤

በፍቅር እስክትመለስ ወንድምህ ናኮርን ከእኔ ዘንድ ተወው፤

ወነሐውር ኵልነ ኀቡረ ምስሌከ፤

ሁላችን ካንተ ጋራ በአንድነት እንሄዳለን አለው።

፲፭፤ወሖረ አብራም እምካራን ወነሥአ ሥራይሃ ብእሲቶ፤

አብራም ሚስቱ ሳራን፤

ወሎጥሃ ወልደ አራን እኁሁ ውስተ ምድረ ከነአን፤

የወንድሙን የአራን ልጅ

ሎጥን ይዞ ከካራን ወደከ ነአን ሄደ፤

ወመጽአ ውስተ ሱር ፤

ወደሱር መጣ፤

ወአንሶሰወ እስከ ሰቂሞን፤

ሰቂሞን ድረስ ተመላለሰ፤

ወኃደረ ውስተ ድርስ ነዋህ፤

በረጅሙ ግራር ሥር አደረ፤

ወርእየ ወናሁ አዳም ጥቀ ምድር ወሙባአ ሐማት እስከ ጎበ ድርስ ነዋህ ፤

ከሐማት መግቢያ ጀምሮ ረጅም ግራር እስከ አለበት ድረስ፤ ምድርዋ እጅግ ያማረች የተወደደች እንደሆ ነች አየ።

፲፰፤ወይቤሎ እግዚአብሔር ለከ ወለዘርዕከ እሁብ ዛተ ምድረ፤

እግዚአብሔርም ይህችን ሀገር ላንተም ለልጆችህም እሰጥህ አለሁ አለው፤

ወሐነፀ አብራም በህየ ምሥዋዐ፤

አብራምም በዚያ መሠዊያን ሠራ ፤

ወአዕረገ ዲቤሁ ጽንሐሐ ለእግዚ አብሔር ዘአስተርአየ፤

ለታየው ለተነጋገረው እግዚ አብሔር በመሠዊያው ላይ ስቡን አቀረበ።

፲፱፤ወተንሥአ እምህየ ወሖረ ውስተ ደብረ ቤቴል ዘመንገለ ባሕር፤

ከዚያም ተነሥቶ በምዕራብ በኩል ወደ አለች ቤቴል ሄደ፤

ወዓጌ ዘመንገለ ጽባሕ፤

በምሥራቅ በኩል ወደአለች ወደ ዓጌ ሄደ፤

ወተከለ ደብተራሁ ህየ፤

ከዝያም ድንኳኑን ተከለ፤

ወርእያ ወናሁ ምድር ስፍሕት ወኄርት ጥቀ፤

ባያትምጊዜ እነሆ የሰፋች፤ የተወደደች ሀገር እንደሆነች አያት፤

ወኵሉ ይሠርዕ ላዕሌሃ፤

ሁሉ በርሷ ላይ ይበቅላል፤

አውያን ወአብላስ ወሮማን ወዕፀ ባላን፤

ወይን፤ በለስ፤ ሮማን፤ ወይ ራው በርሷ ይበቅላል፤

ወድርስ፤

ግራር፣

ወጠርቤንቶስ፣

ቡጥን የሚባል እንጨት፣

ወዕፀ ዘይት፣

የዘይት እንጨት፤

ወቁድሮስ፣

ዋንዛ፣

ወቁጵርስስ ፤

ሰኖባር እንጨት፣

ወሊባኖስ፤

የደጋ እንጨት፣

ወኵሉ ዕፀወ ገዳም፤

በዱር ያሉ እንጨቶች ሁሉ በሷ ይበቅላሉ፤

ወማይ ዲበ አድባር፣

ውሃውም በተራራው ላይ ይፈሳል፤

፳፣ወባረኮ አብራም ለእግዚአብ ሔር ዘአውጽኦ እምነ ዑር ዘከላ ውዴዎን፣

አብራምም ከዑር ከላውዴ ዎን ያወጣው እግዚአብ ሔርን አመሰገነው፤

ወአምጽኦ ውስተዝ ደብር፤ ወደዚህ ተራራ ያመጣውን እግዚአብሔርን አመሰገነው፡፡

፳፩፤ወኮነ በ፩ ዓመት በሱባዔ ሳብዕ በሠርቀ ወርኅ ዘቀዳሚ፤ በአንድ ዓመት በሰባተኛው ሱባዔ በመጀመሪያ ወር መባቻ በሚያዝያ እንዲህ ሆነ፣

ሐነፀ ምሥዋዐ በዝ ደብር፤

በዚህ ተራራ መሠዊያን ሠራ፤

ወፀውአ ስመ እግዚአብሔር፤

የእግዚአብሔርንም ስም ጠራ፤

ወይቤ አንተ አምላኪየ አምላክ ዘለዓለም፤

የዘለዓለም ፈጣሪ አንተ ነህ አለ፣

ወአዕረገ ዲበ ምሥዋዕ ጽንሐሐ ለእግዚአብሔር ከመ የሀሉ ምስ ሌሁ፤

ከሱ ጋራ በረድኤት ጸንቶ ይኖር ዘንድ ለእግዚአብሔር በመሠዊያው ላይ ስቡን አሳ ረገ፣

ወኢይኅድጎ ኵሎ መዋዕለ ሕይወቱ፣

ባለ ዘመኑ ሁሉ እንዳይለ የው፡፡

፭፪፤ወተንሥአ እምህየ ወሖረ መንገለ ደቡብ፤

ከዚያም ተነሥቶ ወደደቡብ ሄደ፤

ወበጽሐ እስከ ኬብሮን፤

እስከ ኬብሮንም ደረሰ፤

ወኬብሮን አሜሃ ተሐንፀት፤

ኬብሮንም ያን ጊዜ ተሠራች፣

ወነበረ ህየ ዓመተ ፪ተ፤

ሁለት ዓመት ከዝያ ተቀመጠ፤

ወሖረ ውስተ ምድረ ደቡብ እስከ ቦአ ሎጥ፤

ሎጥ እስኪገባ ድረስ ወደ ደቡብ አገር ሄደ።

፭፫፤ወኮነ ዓባር ዲበ ምድር፤

በዓለም ሁሉ ረኃብ ሆነ፤

ወሖረ አብራም ውስተ ግብጽ በሣልስ ዓመት ዘሱባዔዝ፤

በዚህ ሱባዔ በሶስተኛው ዓመት አብራም ወደግብጽ ሄደ፤

ወነደረ ውስተ ግብጽ ፭ዓመተ ዘእንበለ ትትሐየድ ብእሲቱ እም ኄሁ፤

ሚስቱ ከሱ ሳትለይ አምስት ዓመት በግብጽ ኖረ፤

ወጣይናስ ዘግብጽ አሜሃ ተሐንፀት በ፮ከረምት እምድኅረ ኬብሮን፤

በግብጽ ያለች ጣይናስም ያን ጊዜ ከኬብሮን በኋላ በሰባት ዓመት ተሠራች።

፭፬፤ወኮነ እመ ሄደ ፈርዖን ሶራይሃ ብእሲቶ ለአብራም ቀሠፈ እግዚእብሔር ፈርዖንሃ፤

የአብራም ሚስት ሶራይን በቀማው ጊዜ እግዚአብሔር ፈርዖንን በመከራ ቀሰፈው፤

ወኮሉ ቤቶ በመቅሠፍት ዓቢይ በእንተ ሶራ ብእሲቱ ለአብራም ፤ የአብራምን ሚስት ሶራን ስለወሰደ ወገኑን ሁሉ በጽኑ መቅሠፍት ቀሠፋቸው።

፭፭፤ወአብራም ክቡር ጥቀ በጥሪት፤

አብራምም በገንዘብ እጅግ የከበረ ነበር፤

በዓባዕዕ ወአልህምት ወበአእዱግ ወበአፍራስ ወበአግማል ወበአግብርት ወበአዕማት በወርቅ ወበብሩር ፈድፋደ፤

አብራምም በበግ በላም በፈረስ በአህያ በግመል በወንድ

ባርያ በሴት ባርያ በወርቅ በብር እጅግ የከበረ ነበረ፤ ወሎጥኒ ወልደ እኁሁ በጥሪት ከማሁ፤

የአብራም የወንድሙ ልጅ ሎጥም በገንዘብ እንደ እርሱ የከበረ ነበር።

፭፤ ወአግብአ ፈርያን ሶራይሃ ብእሲቶ ለአብራም ፤

ፈርያንም የአብራምን ሚስት ሶራን መለሰ፤

ወፈለሰ እምድረ ግብጽ ወሖረ ውስተ መካን ኀበ ተከለ ደብተራሁ እንተ ቀዲሙ ውስተ መካነ ምሥዋዕ ዘዓጌ እምጽባሐ ቤቴል ወባሕር፤

አብራምም ከግብጽ ተነሥቶ በቤቴል ምሥራቅና በምዕራብ መካከል፤ ቀድሞ ድንኳን ተክሎበት ወደነበረ በዓጌ ወደአለው ቦታ ሄደ።

፰፤ወባረኮ አብራም ለእግዚአብሔር አምላኩ ዘሜጦ በሰላም፤ አብራምም በፍቅር የመለሰው እግዚአብሔርን አመሰገነው፤

፱፤ ወኮነ በዘሃ ወቅ ኢዮቤልዩ በሣልስ ዓመ ዘሱባዔ ቀዳሚ ዓብአ ውስተዝ መካን፤

በዐርባ አንደኛው ኢዮቤልዩ በመጀመሪያው ሱባዔ በሚቆጠር በሦስተኛው ዓመት እንዲህ ሆነ አብራም ወደ ዚህ ቦታ ተመለሰ፤

ወአዕረገ በዲቤሁ ጽንሐሐ፤

በላዩ ላይ ስቡን ሠዋ፤

ወፀውዐ ስመ እግዚአብሔር፤

የእግዚአብሔርን ስም ጠራ፤

ወይቤ አንተ እግዚአብሔር አምላክ ልዑል አምላኪየ ለዓለመ ዓለም፤

የዘለዓለም ፈጣሪየ ገናና ልዑል እግዚአብሔር አንተ ነህ አለ።

፲፱፤ወበራብዕ ዓም ዘዝሱባዔ ተፈልጠ ሎጥ አምኔሁ፤

በዚህ ሱባዔ ባራተኛው ዓመት ሎጥ ከሱ ተለየ፤

ወኃደረ ሎጥ ውስተ ሰዶም፤

ሎጥም በሰዶም ኖረ፤

ወሰብአ ሰዶምሰ ኃጥአን ጥቀ፤

የሰዶም ሰዎች ግን እጅግ ሕገ እግዚአብሔርን የዘነጉ ነበሩ፤

ወኃዘነ ልቡ እስመ ተፈልጠ ወልደ እትሁ እምኔሁ፤

የወንድሙ ልጅ ሎጥ ከሱ ተለይ ቶአልና ልቡ አዘነ፤

እስመ አልቦ ውሉድ በውእቱ ዓመት አመ ተዜወወ ሎጥ፤

ሎጥ በተማረከ ጊዜ በዝያ ወራት ልጅ አልነበረውምና፤

፴፤ወይቤሎ እግዚአብሔር ለአብራም እምድኅረ ተፈልጠ እምኔሁ ሎጥ በራብዕ ዓመት ዘሱባዔዝ ፤

በዚህ ሱባዔ ባራተኛው ዘመን ሎጥ ከሱ ከተለየ በኋላ አብራምን እግዚአብሔር እንዲህ አለው፤

ወይቤሎ አንሥእ አዕይንቲከ እመካን ወአደ ሀለወከ ትንበር ዝየ መንገለ ሰሜን ወሊባ ወባሕር ወጽባሕ፤

ትቀመጥበት ዘንድ ካለህበት ቦታ አንገትህን አቅንተህ አራቱን ማዕዘን ተመልከት አለው፤

እስመ ኵላ ምድረ እንተ ትሬኢ ለከ ወለዘርዕከ እሁብ እስከ ለዓለም፤

ይህችን የምታያትን አገር ላንተም ለልጆችህም ለዘለዓለሙ፤ እሰጥህአለሁና።

፴፭፤ወአሬሲ ዘርዐከ ከመ ኖፃ ባሕር፤

ልጆችህን እንደ ባሕር አሸዋ አደርጋቸዋለሁ፤

ወአመ ይክል ሰብእ ጕልቆ ኖፃ ባሕር፤

ሰው የምድርን አሸዋ መቁጠር ቢቻለው፤

ወዘርእከኒ ይትኤለቁ፤

ልጆችህም ይቆጠራሉ፤

ያም አይቁጠር ይኸም አይቁጠር ማለት ነው።

ተንሥእ ወአንሶሱ ውስተ ኵኃ ወርኀባ፤

ተነሥተህ ወርዷን ቁመቷን ዙራት፤

ወርኢ ኵሎ እስመ ለዘርእከ እሁባ፤

ለልጆችህ እሰጣታለሁና ሁሉን ተመልከት አለው።

፴፱፤ወሖረ አብራም ኬብሮን ወነ ደረ ህየ፤

አብራምም ወደኬብሮን ሂዶ ተቀመጠ።

፴፫፤ወበዝ ዓመት መጽአ ኮሎዶ ጎምር ንጉሠ ኤላም፤

የኤላም ንጉሥ ኮሎዶጎሞር በዚህ ዓመት መጣ ፤ ወአግልፋል ንጉሥ ዘሰናያር፤

የሰናያር ንጉሥ አግልፋል፤

ወአሪአክ ንጉሠ ሲላስር፤

የሲላስር ንጉሥ አሪአክ፤ እነዚህ ነገሥታት ሁሉ በዝያ ወራት መጡ፤

ወቴርጋል ንጉሠ አሕዛብ፤

የአሕዛብ ንጉሥ ቴርጋልም መጣ፤

ሐተታ የቀሩትስ ምነው የአሕዛብ ነገሥታት አይደሉም? ቢሉ በእነዚህ ይጸና ልና እንዲህ አለ፤

ወቀተልም ለንጉሠ ሰዶም፤

እነዚህ የሰዶምን ንጉሥ ወጉት።።

፴፬፤ወጐየ ንጉሠ ሰዶም ባላቅ፤

የሰዶም ንጉሥ ባላቅ ድል ተነሥቶ ሸሸ ፤

ወብዙኃን ወድቁ በቍስል፤

ብዙ ሰዎች በጦር ቆስለው ወደቁ፤

በሴላስዬማው ብሔረ ዔው፤

የጨው ሀገር፤ በሚሆን በዚህ ጦር ቆስለው ወደቁ፤ አንድም ስለሴሌሴዬማው ይላል ፤

ወዔወዉ ሰዶምሃ ወአዳማሃ ወሶቤኤም፤

ሰዶምን አዳማን ሶቤኤምንም እነዚህን አገሮች ወረራቸው ዘረፏቸው፤

ወዔወውም ለሎጥሂ ወልደ እኁሁ ለአብራም ወሎሉ ጥሪቶ ወሐረ እስከ ዳን፤

የአብራም የወንድም ልጅ ሎጥን ገንዘቡን ሁሉ ማር ከው እስከ ዳንም ድረስ ሔዱ፤

፴፭፤ ወመጽአ ዘድኅነ እምዔዋዊ ፩ዱ ብእሲ ጎበ አብራም ወነገሮ ለአብራም ከመ ተዔወወ ሎጥ ወልደ እኁሁ፤

ከጦር ድኖ የመጣ አንድ ሰው የወንድሙ ልጅ ሎጥ እንደተማረከ ለአብራም ነገ ረው፤

ወሎሉ ጥሪቱ፤

ገንዘቡም ሁሉ
ወአስተረሰየ አብራም ልደ ቤቱ፣
አስጠረረ አስጌጠ ብትል ይሆ
ናል፣ አብራምም ቤተ ሰብሞ
ቹን አሽከሮቹን ቆጥሮ አስታ
ጥቆ ሎጥ ወደተማረከበት
ተነሥቶ ሄደ፣

ወሠርዓ ዲበ ርዕሱ አብራም
ወዲበ ዘርዑ አሥራተ ቀዳሜ
ለእግዚአብሔር፣

አብራምም ነገሥተ ኮሎዶጎ
ሞርን ድል ነሥቶ ሎጥን
ይዞ ከተመለሰ በኋላ በሱም
በልጆቹም ከገንዘባችሁ አሥ
ራቱን በኵራቱን አውጥታ
ችሁ ለእግዚአብሔር ስጡ
ብሎ ሥርዐት ሠራ፣

አንድም ወአስተረሰየ ልደ
ቤቱ ሖረ ወቀተሎ ለኮሎዶ
ጎምር ወተመይጠ ወአሠሮ
ለመልከጼዲቅ ይላል አብነት፣
ወእግዚአብሔር ሠርዐ ሥርዓተ
ለዓለም ከመ ያህብሙ አሥ
ራተ ለካህናት ለእለ ይትቀነዩ በቅ
ድሜሁ ከመ የአኃዝሙ ለዓለም ፣
እግዚአብሔርም ለዘለዓለም
ገንዘብ አድርገው ይይዙት
ዘንድ በፊቱ ለሚአገለግሉት
ለካህናት ይሰጣቸው ዘንድ
ለዘላለሙ ሥርዐቱን ሠራ።

፴፮፤ወአልቦ ለዝ ሕግ ወሰነ
መዋዕል እስከ ትውልድ ዘለዓ
ለም ሠርፆ፤

ለዚህ ሕግ የተወሰነ ዘመን
የለውም፣ እስከ ልጅ ልጅ
ለዘለዓለሙ ሥርዓት አድርጎ
ሠራው እንጅ፤

ከመ የሀቡ አሥራተ እምኵሉ
ለእግዚአብሔር፤

ከገንዘቡ ሁሉ አሥራቱን ለእ
ግዚአብሔር ይሰጡ ዘንድ፣
እምዘርዕ ወእምወይን ወእም
ቅብዕ ወእምአልህምት ወእምአባ
ግዕ ወእምአጣሊ፤

ከዘሩ ከወይኑ፣ ከዘይቱ
ከላሙ ከበጉ ከፍየሉ የዚህን
ሁሉ አሥራት ለእግዚአብ
ሔር ይሰጡ ዘንድ ሥርዓት
አድርጎ ሠራ።

፴፯፤ወውእቱ ወሀበ ለካህናቲሁ
ለበሊዕ ወለሰትይ በፍሥሐ በቅ
ድሜሁ፤

እሱም በፊቱ ደስ እያላቸው
ይበሉት ይጠጡት ዘንድ ለካ
ህናት ሰጣቸው።

፴፰፤ወበጽሐ ኀቤሁ ንጉሠ ሰዶም
ወሰገደ ቅድሜሁ ለአብራም፤

የሰዶም ንጉሥ ደርሶ በአብራም ፊት ሰገደ፤

ወይቤ እግዚእነ አብራም ጸግወነ ነፍሰ እለ ባሳሕከ፤

ጌታችን አብራም ! ያዳንኸውን ሰው ስጠን አለ፤

ወምሕርካሁሰ ይኩን ለከ፤

ምርኮው ግን ላንተ ይሁን፤

እስመ ኢይከውን ብሔር ዘእንበለ ነፍስ፤

ሀገር ያለ ሰው አይሆንም አይጸናምና ያዳንከውን ሰው ስጠን፤

፴፱፤ወይቤሎ አብራም ሎቱ አነሥአ እደውየ ወአሌዕል ውስተ ሰማይ ኀበ አምላክ ልዑል እም ፊትል እስከ ቶታነ አሣዕን ጥቀ ከመ ኢይነሥአ እምኵሉ ዘዚአክ፤

አብራምም እሱን እንዲህ አለው እጄን ገናና ወደሆነ ፈጣሪዬ ከፍ ከፍ አደርጋለሁ ካንተ ገንዘብ ሁሉ ከፊትል ጀምሮ እስከ ጫማ ማዘቢያ ድረስ እንዳልቀበል፤

ከመ ኢትኩን በሀሌ አነ አብአልክሆ ለአብራም፤

አበዓልክሆ ለአብራም ይላል አብነት አብራምን እኔ አከበርኩት አገነንኩት እንዳትል፤

ዘእንበለ ዘበልዑ ዳዕሙ ደቂቅየ ወራዙት፤

እነዚያ ጕልማሶች ከበሉት በቀር የተበላ አይመለስ፤ የፈሰሰ አይታፈስ እንዲሉ፤

ወባሕቱ ይንሥኡ ዕደው እለ ሖሩ ምስሌየ አውናን ወኤስኬል ወመምሬ እሙንቱ ወይኩን መክፈልተ ለእሉ ዕደው፤

ከእኔ ጋራ አብረውኝ የዘመቱ አውናን ኤስኬል መምሬ እነዚህ ፈንታቸውን ይውሰዱ እንጅ፤ ከአንተ ገንዘብ ሁሉ ከፊትል ጀምሮ እስከ ጫማ ማዘቢያ ድረስ እንዳልቀበል እጄን ልዑል ወደ ሆነ ፈጣሪዬ ከፍ ከፍ አድርጌ እምላለሁ አለው፤

ምዕራፍ ፲፪

፩፤ወእምድኅረዝ ነገር በራብዕ ዓመት ዘገሠ ሱባዔ በሠርቀ ወርኀ ኅልስ ኮነ ቃለ እግዚ አብሔር ኀበ አብራም በሕልም፤

ከዚህም ነገር በኋላ በዚህ ሱባዔ ባራተኛው ዘመን